ምዕራፍ ፩
ጉባኤ

፩ ፤ ወሞተ : ረዓይትኒ : እንተ፡ ኀበ : ወጽኡ : መናፍስት : እምነ : ነፍስተ ሥጋሆሙ ።።
ከደቂቀ : ሴት : የተወለዱ : በየ ወጡበት : የሚሆን : የረዓይት ሞታቸው፡
፪ ፤ ለይኩን : ዘይማስን ፤
ሙሱን : ሞት : ነው ፤ እንድም : ከደቂቀ : ሴት : የተወለዱ : በየወ ጡበት : የሚሆን : የረዓይት : ሞታቸው : ሥጋቸው : ይፈርስ : ይበሰብስ : ዘንድ : ነው ፤ አን ድም : ከደቂቀ : ሴት : የተወለዱ : የረዓይት፡ሞታቸው በየወጡበት : ነው ፤ ያው : ግን : ሥጋቸው : የሚፈርስ : የሚበሰብስ : ይሆን : ዘንድ : ነው ፤
፫ ፤ ወዘእንበለ : ይኩን : ኵነኔ : ከማሁ : ይማስኑ : እስከ : ዕለተ : ኵነኔ : ዓባይ፤
እስከ : ዕለተ : ተፍጻሜት : ዓባይ : ሲል : ነው ፤ ፍጹም : ፍርድ : ሳይሆን : እስከ : ዕለተ : ምጽአት ፤
እንዲሁ : ይጠፋሉ ፤
እምዓለም : ዓቢይ ፤
ዓለም : ገሃነም : ለኃጥአን : ከመሰ ጠቱ : አስቀድሞ ፤
ይትፌጸም : እምትጉሃን : ወረሲዓን፡
በደቂቀ : ሴት : ፍጹም : ፍርድ ይፈጸማል ፤
፬ ፤ ወይእዜኒ : ለትጉሃን : እለ : ፈነውከ : ትስአል : በእንቲአሆሙ : እለ : ቀዲሙ : በሰማይ : ሀለዉ ፤
በሎሙ : ያለበት : ነው ፤ አሁንም : ለእነርሱ : ልትለምንላቸው ፤ የላኩህን : ከዚያ : አስቀድሞ : በደብር : ቅዱስ : የነበሩ : ለኃጢ አት : የሚተጉ : ደቂቀ : ሴትን : እንዲህ፡በላቸው ፤
፭ ፤ ወይእዜኒ : አንትሙ : በሰ ማይ : ሀለውክሙ ፤
ዛሬም : በልዑል : መዓርግ : በደ ብር : ቅዱስ : በሰማያዊ : ግብር፡ አላችሁ ፤
ወኀቡዓት : ዓዲ : ኢተክሥቱ : ለክሙ ፤
ምሥጢረ : ኃጣውዕ : ምሥጢረ አጋንንት : አልተገለጡላችሁም ፤
፮ ፤ ወምኑን : ምሥጢረ : አእመ ርክሙ : ወዘንተ : ዜነውክሙ : ለአን ስት : በጽንአ : ልብክሙ፤
የተናቀ : ምሥጢርንም : አወቃ ችሁ ፤ በልቡናችሁም : ጽናት : ይህን : ነገር : ለሴቶች : ነገራችሁ ፤
፯ ፤ ወበዝንቱ : ምሥጢር : ያበዝኃ : አንስት : ወሰብእ : እኪተ : ዲበ : ምድር : በሎሙ : እንከሰ : አል ብክሙ : ሰላም ፤
ከላይ : በሎሙ : እንዳለ : በዚህ : ይታወቃል ፤ በዚህም : ምሥጢር :

በወንዶችና : በሴቶች : በዚህ : ዓለም : ክፋትን : ያበዛሉ ፤ እንግዲህስ : ፍቅር : አንድነት : የላች ሁም : በላቸው : አለኝ ።

፮ ፤ ወነሥኡኒ : ውስተ : ፩ዱ : መካን : ጎበ : ሀለዉ : ህየ : ከመ : እሳት : ዘይነድድ ።

እንደ : እሳት : የሚነድ : ደቂቀ ሴት : ወደአሉበት : አንድ : ቦታ : ወሰዱኝ : አለ ፤ መካነ : ኃጥአን ። አንድም : ስነ : ፍጥረት ፤

ወሰበ : ይፈቅዱ : ያስተርእዩ : ከመ ሰብእ ።

ከመ : እሳት : ብሎ : ነበርና : ሰምች : ናቸው : ለማለት : እንደ : ሰው : ይታያሉ : አለ ። አንድም : ለንጻሬ : የበቁ : ጻድቃን : ሊያዩዋቸው : በወደዱ : ጊዜ : እንደ : ሰው : ያዩዋቸዋል ፤

፱ ፤ ወወሰዱኒ : ውስተ : መካን : ዘአውሶ : ወውስተ : ደብር : ዘከተማ : ርእሱ : ይበጽሕ : እስከ : ሰማይ ፤

ጥልቅ : ነፋስ : ወዳለበት : ቦታ ወሰዱኝ ። ጫፉ : እስከ : ሰማይ : የሚደርስ : ተራራ : አየሁ ። ስነ : ፍጥረት : ነው ። አንድም : መካነ : ኃጥአን : ላገኛቸው : መከራ : ፍጻሜ : እንደ : ሌለው : ለማጠየቅ ።

፲ ፤ ወርኢኩ : ፬ተ : መካናተ : ብሩሃተ ።

አንድ : መካነ : ኃጥአንን ። ሦስቱን : መካነ : ጻድቃንን : አየሁ ። ሦስት : አለ : ባለ : መቶ ፣ ባለስሳ ፣ ባለ : ሠላሳ : ስለኖረባት ። አንድም : ወጣኒ ፣ ማዕከላዊ ፣ ፍጹማዊ : ስለኖረባት : መካነ : ኃጥአንን : ብሩህ : አለው : በጻድቃን : አስጠግቶ ።

ወነጐድጓድ : ውስተ : አጽናፍ ።

በመካነ : ጻድቃን : አጠገብ : ባለ : በመካነ : ኃጥአን : ነጐድጓድ : አለ ።

ወጎበ : ዕመቁ : ቀስተ : እሳት ፤

በጥልቀነቱ : ዘንድ : ቀስተ : እሳት : አለ ።

ወሐፅ : ወምጕንጻቲሆሙ ።

የኃጥአን : ጕራንጕሬያቸው : አለ ። ሰይፈ : እሳት : መባርቅት አለ ፤ መቅሠፍተ : ኃጥአንን : በምሳሌ : ያሳየዋል ።

ወሰይፈ : እሳት : ወመባርቅት : ኵሉ ።

የእሳት : ሰይፍ : መብረቆችም ሁሉ : አሉ ።

፲፩ ፤ ወነሥኡኒ : እስከ : ማየ : ሕይወት : ዘይትናገር ።

ድምጽ : ያለው : የመጣያ : ውኃ : ወዳለበት ። አንድም : ዘይትነገር : ቢል : በኔ : ቃል : የሚነገር : ማየ : ሕይወት : እስካለበት : ድረስ ። አንድም : በሰው : አድሮ : የሚናገር : ማየ : ሕይወት : መንፈስ : ቅዱስ ። አንድም : ዘይትነገር : በኔ : ቃል : የሚነገር : ማየ : ሕይወት : መንፈስ : ቅዱስ : እስከሚሠጥበት : ዘመን : ድረስ : አደረሱኝ ።

ወእስከ : እሳተ : ዓረብ ፤

በምዕራብ : እስከ : አለው : ብርሃን : ድረስ : ወሰዱኝ :
ዘውእቱ : ይእኀዝ : ኵሉ : ዕርበተ : ፀሐይ ፤
ይኸውም : የፀሐይን : መግቢያ ሁሉ : የሚይዝ : ነው ፤
፲፪ ፤ ወመጻእኩ : እስከ : ፈለገ : እሳት : ዘይውኅዝ : እሳቱ : ከመ : ማይ ፤
እሳቱ : እንደ : ፈሳሽ : ውኃ : ሆኖ : ውቅያኖስ : ሲገባ : ያየዋል ፤ ስነ : ፍጥረት ፤ አንድም : መካነ : ኃጥ
አን : ሳገኛቸው : መከራ : ፍጻሜ : እንደሌለው : ለማጠየቅ ፤
ወይትከለው : ውስተ : ባሕር : ዓቢይ : ዘመንገለ : ዓረብ ፤
በምዕራብ : ወዳለው : ባሕር : ሲፈስስ : አየሁ ፤
፲፫ ፤ ወርኢኩ : ኵሉ : ዓበይተ : አፍላገ : ወእስከ : ዓቢይ : ጽልመት በጸሐኩ ፤
ጽኑ : ጨለማ : በርባሮስ : እስካ ለበት : ድረስ : ደርሼ : ታላላቅ : ወንዞችን : ሁሉ : አየሁ ፤
ወሖርኩ : ኀበ : ኵሉ : ዘሥጋ : ያንሶሱ ፤
ሥጋዊ : ደማዊ : ሁሉም : ወደ ሚመላለስበት : ሄድኩ ፤
፲፬ ፤ ወርኢኩ : እድባረ : ቆባራት ዘክረምት ፤
በክረምት የሚገኙ : ጭጋጎች : ያሉባቸው : ተራሮችን : አየሁ ፤
አንድም : በክረምት : የሚገኝ : የጉም : ተራራ : አየሁ ፤
ወምክዓወ : ማይ : ዘኮሉ : ቀላይ ፤
ውኃ : የሚፈስበትን : ሁሉ : አየሁ ፤
፲፭ ፤ ወርኢኩ : አፋሆሙ : ለኵሉመ አፍላግ : ምድር ፤
የዚህ : ዓለም : ውኃ : ሁሉ : የሚገባበትን ፤
ወአፋሃ : ለቀላይ ፤
ውቅያኖስ : የምትቀበልበትን : አየሁ ፤
፲፮ ፤ ወርኢኩ : መዛግብተ : ኵሉ : ነፋሳት ፤
አራቱ : ነፋሳት : የሚወጡበትን : የሚገቡበትን : አየሁ ፤
ወርኢኩ : ከመ : ቦሙ : አሠርገወ : ኵሉ : ፍጥረተ ፤
አጽንዓ : ሲል : ነው ፤ በሳቸው : ፍጥረትን : ሁሉ : እንዳጠና : አየሁ ፤
ወመሠረታቲሃ : ለምድር ፤
የምድርን : መሠረት : አየሁ : አለ ፤ ክታች : ነፋስ ፤ ቀጥሎ : እሳት ፤ ቀጥሎ : ውኃ ፤ ቀጥሎ : መሬት ነውና ፤
፲፯ ፤ ወርኢኩ : ዕብነ : ማዕዘንተ ምድር ፤
ምድር : የጸናበት : በአራቱ : ማዕዘን : ያለ : አድማስን : አየሁ ፤
ወርኢኩ : ፀተ : ነፋሳተ : እለ : ይፀውርዋ : ለምድር ፤
ምድርን : እንደ : ካስማ : የያዟትን ፤ አራቱን : ነፋሳት ፤
ወለጽንዓ : ሰማይ ፤
ጽንዕት : ሰማይ : ሲል : ነው ፤

ሰማይ : የጸናበትንም : አራቱን ነፋሳት : አየሁ ።

፲፰ ። ወርኢኩ : ከመ : ነፋሳት : ይረብብዋ : ለልዕልና : ሰማይ ።

ልዕልት : ሲል : ነው ። ልዕልት ሰማይን : እንደ : ካስማ : የያዟት : ነፋሳትን : እንደ : ምሰሶ : ሁነው : አየሁ ።

፲፱ ። ወእሙንቱ : ይቀውሙ : ማዕከለ ሰማይ : ወምድር ።

ከእነሳቸውም : በምድርና : በሰማይ : መካከል : እንደ : አዕማድ : (ምሰሶዎች) : ሁነው : ቁመው : አየሁ ።

ወእሙንቱ : ውእቶሙ : አዕማደ : ሰማይ ።

እነሳቸውም : የሰማይ : ምሰሶዎች ናቸው ።

፳ ። ወርኢኩ : ነፋሳተ : እለ : ይመ ይጥዋ : ለሰማይ ።

ሰማይን : የሚሸከሙ : ነፋሳትን አየሁ ።

ወእለ : ያወርቡ : ክበበ : ፀሐይ : ወኮሎ : ከዋክብተ ።

ፀሐይን : ከዋክብትን : የሚያገቡ : ነፋሳትን : አየሁ ።

፳፩ ። ወርኢኩ : ዘዲበ : ምድር : ነፋሳተ : ዘይፀውሩ : ደመናተ ።

በዚህ : ዓለም : ደመናትን : የሚሸከሙ : ነፋሳትን : አየሁ ።

፳፪ ። ወርኢኩ : ፍናወ : መላእክት ። ጉልቈ : መላእክት : ሲል : ነው ። የመላእክትንም : ቍጥር : አየሁ ።

ወርኢኩ : ውስተ : ጽንፈ : ምድር : ጽንዐ : ዘሰማይ : መልዕልተ ።

ጠፈር : በላይ : ሆኖ : የጸናበትን : አድማስን : አየሁ ። አንድም : በላይ : ሁኜ : ጠፈር : የጸናበት : አድማስን : አየሁ ።

፳፫ ። ውኀስፍኩ : መንገለ : አዜብ : ወይነድድ : መዓልተ : ወሌሊተ : ጎበ ፯ቱ : አድባር : ዘእምዕብን : ክቡር ።

ውኀስፍኩ : መንገለ : አዜብ : ጎበ : ፯ቱ : አድባር : ዘእምዕብን ክቡር : ዘይነድድ : መዓልተ : ወሌሊተ : ሲል : ነው ። በመዓልትም : በሌሊትም : የሚያበራ : ነው ። ከከበረ : በአዜብ : እኩል : ወዳለ : ተራራ : ሄድኹ ። አንድም : የዕንቍ : ተራራ : ወዳለበት : ሄድኹ ።

፳፬ ። ፫ቱ : ዘመንገለ : ጽባሕ : ወፍቱ : ዘመንገለ : አዜብ ።

ሦስቱ : በምሥራቅ : በኩል ። ሦስቱ : በዓዜብ : በኩል : ናቸው ። ወዘመንገለ : ጽባሕሰ : ዘእምዕብነ : ኀብር ።

ከሦስቱ : አንዱ : ብዙ : መልክ ካለው : ዕንቍ : ወገን : ነው ። ወ፩ዱ : ዘእምዕብነ : ባሕርይ ።

አንዱ : ባሕርይ : ከሚባል ። ወአሐዱኒ : ዘእምዕብነ : ፈውስ ። አንዱ ። ደመ-ረጭ ። (ደመአርድ): የሚባል ዕንቍ : ያለበት : ነው ። ወዘመንገለ : አዜብ ።

በምዕራብ : በኩል : ያለው : ሦስቱ : ሁሉ ፤
እምዕብን : ቀይሕ ፤
የቀይ : ዕንቊ : ተራራ : ነው ፤
አንድም : ቀይ : ዕንቊ : ያለበት ተራራ : ነው ፤
፳፩ ፤ ወማዕከላይሰ : ይጕድዕ : እስከ : ሰማይ : ከመ : መንበሩ : ለእግዚአብሔር : ዘእምዕብነ : ፔካ ፤
ወማዕከላይሰ : ዘእምዕብነ : ፔካ : ሲል : ነው ፤ ፔካ : ከሚባል : ዕንቊ : ወገን የሚሆን : መካከለኛው : ተራራ ፤ ይጕድዕ : ይበጽሕ : ይለክፍ : እስከ : ሰማይ : ሲል : ነው ፤ እስከ : ሰማይ : ይደርሳል ፤ ከመ : መንበሩ : ሲል : እንደ : እግዚአብሔር : ዙፋን ፤ አንድም : የእግዚአብሔር : ዙፋን ፣ መቀመጫ : እንደመሆኑ : እስከ ሰማይ : ይደርሳል ፤
፳፪ ፤ ወድማሁ : ለመንበሩ : ዘእምዕብነ : ሰንፔር ፤
ድማሁ : ለመንበር ፣ አጕበሩ : ሰንፔር : ከሚባል : ዕንቊ : ወገን : ነው ፤
ወእሳተ : ዘይነድድ : ርኢኩ : ዘሀሎ ውስተ : ኵሉ : አድባር ፤
በተራራ : ሁሉ ፡፡ ያለ : የሚነድ እሳትንም : አየሁ : አለ ፣ በሰባት : ተራራ : የሚያበራ : ዕንቊ : አየሁ ፤ ለጊዜው : እንዲህ : ያለ : አይታል ፤ ለኋላው : ምሳሌ : ነው ፤ ስድስት : ተራራ : የዓለመ : ፍጡራን ፤ ዘእምዕብነ : ጎበር : ያለው : ከብዙ : ሪም : ያላቸው : ጻድቃን : እንደ : ዮሐንስ : እርሱ : ከነቢያት : ነቢይ ፣ ከደናግል : ድንግል ፣ ከሰማዕታት : ሰማዕት ፣ ከሐዋርያት : ሐዋርያ : ነውና ፤ ባሕርይ : ሳይበድሉ : የቀሩ : እንደ : ኤልያስ : እንደ : ኤርምያስ : ያሉት ፤ ቀደስኩከ : እምከርሠ : እምከ : ወዘእንበለ : ትጸእ : እማኅፀን : ሜምኩከ[ዲ] : እንዲል ፤ ዘእምዕብነ : ፈውስ : በድለው : የተመለሱ : እንደ : አዳም ፣ እንደ : ዳዊት ፣ እንደ : ጴጥሮስ : ያሉት ፤ ቀይሕ : ያለው : ሰማዕታት ፣ ደማቸውን : ያፈሰሱ ፣ ከእሳት : ይወድቃሉና ፤ ማዕከላይ : ያለው : የዓለመ : ፈጣሪ ፤ ይበጽሕ : አለው ፣ ከዓለመ : ፍጡራን : ዓለመ : ፈጣሪ : ይበልጣልና ፤ አንድም : ስድስቱ : በ፮ቱ : ቃላተ : ወንጌል : ያመኑ : ምዕመናን ፤ ማዕከላይ : ይበጽሕ : ያለው ፣ የእመቤታችን ፣ የእግዚአብሔር ማደሪያ : እንደ : መሆንዋ : መልዕልተ : ፍጡራን : መትሕተ : ፈጣሪ : ናትና ፤
፳፫ ፤ ወርኢኩ : ሀየ : መካነ : ማዕዶቱ : ለዓቢይ : ምድር ፤ የአድማስ : መጨረሻ : ውቅያኖስን አየሁ ፤
ሀየ : ይትጋብኡ : ማያት ፤ ውኃዎች : በዚያ : ይሰበሰቡበታል ፤
፳፬ ፤ ወርኢኩ : ንቅዓተ : ምድር : ዕሙቀ : በአዕማዲሁ : ለእሳተ : ሰማይ ፤ በሰማይ : እሳት : ምሰሶዎች : ጥልቅ : የሆነ : የምድር : ጉድ

ፀ ኤር. ፩፡፩ ፤

ጓድ : አየሁ : አለ ፣ በሰማይ : እሳት : የሚቃጠሉ : ደቂቀ : ሴት : ያሉበት : ጥልቅ : የሚሆን : ገዛነ ምንም : አየሁ ፤

፳፱ ፤ ወርኢኩ : በውስቴቶሙ : አዕማደ : ሰማይ : ዘእሳት : ዘይወርዱ ፣ በእሳት : የሚቃጠሉ : ወደጥል ቅም : የሚወርዱ : በውስጣቸው : ደቂቀ : ሴትን : አየሁ ፤

ወአልቦሙ : ጕልቍ : ኢመንገለ : መል ዕልት : ወኢመንገለ : ዕመቅ ፣ ስፍር : ቍጥር : የላቸውም ፤ አንድም : ለሚያገኛቸው : መከራ ፍጻሜ : የለውም ፤ አንድም : መልዕልት : ወደላይ : ሰማይ : ወደታች : መሠረት : የለውም ለሚያገኛቸውም : መከራ : ፍጻሜ : እንደሌለው : ለማጠየቅ ፤

፴ ፤ ወዲበ : ውእቱ : ንቅዓት : ርኢኩ : መካነ ፣ በጕድጓዱ : ላይ : ቦታ : አየሁ ፤

ወኢጸንዓ : ሰማይ : ላዕሌሁ : ወኢመ ሠረተ : ምድር : በታሕቴሁ ፣ ወደ : ላይ : ጠፈር ፣ ወደታች መሠረት : የለውም : ለሚያገኛ ቸውም : መከራ : ፍጻሜ : እንደ ሌለው : ለማጠየቅ ፤

፴፩ ፤ ወኢማይ : አልቦ : ላዕሌሁ : ወኢአዕዋፍ : አላ : መካነ : በድው : ውእቱ ፣ ምድረ : በዳ : ነው : እንጂ ፣ ውኃ : አዕዋፍ : የሉበትም ፤ አንድም : ከረድኤት ፣ ከጻድቃን ፣ ከመላ እክት : ምድረ : በዳ : ነው : እንጂ ፣ ረድኤት ፣ መላእክት ፣ ጻድቃን ፣ የሉበትም ፣

፴፪ ፤ ወግሩመ : ርኢኩ : በህየ : ጌተ : ከዋክብተ : ከመ : ዓበይት : አድባር : ዘይነድዱ ፤

እሳት : እንደ : ተያያዘው : ተራራ : የሚነዱ : ሰባት : ከዋክብትን : አየሁ : አለ ፣ ደቂቀ : ሴትን : አየሁ ፤

ሰብእተ : አላቸው ፣ በፍጹም : ቁጥሮ : ነው ፤ ከዋክብት : አላ ቸው ፣ በጥንተ : ግብራቸው : ነው ፤ ከዋክብትን : ያመልኩ : ነበርና ፤

፴፫ ፤ ወከመ : መንፈስ : ዘይሴአ ለኒ : ይቤ መልአክ ፣ የሚጠይቀኝ : መልአክ : ባልደረ ባዬ : እንደመሆኑ : እንዲህ : አለ ፤

ዝውእቱ : መካነ : ተፍጻሜቱ : ለሰ ማይ : ወለምድር ፤

ይህ : ቦታ : የምድርና : የሰማይ መጨረሻ : ቦታ : ነው : አለ ፣

፴፬ ፤ ቤተ : ሞቅሕ : ኮኖሙ : ዝንቱ ፤

የሰማይ ፣ የምድር : ፍጻሜ : የሚሆን : ይህ : ቦታ : ለደቂቀ : ሴት : የግዞት : ቦታ : ሆናቸው ፤ የሚያሳየው : በመጨረሻው : በምዕራብ : ነውና ፤ አንድም : የሰማይ ፣ የምድር : ፍጻሜ : የሚሆን : ሰማይ : ያይደለ ፣ ምድርም : ያይደለ : ይህ : ቦታ ቤተ : ግዞት : ሆናቸው ፤ በጎ

ዋው : ሁነው : ያሳየዋልና ፤ ለከ ዋክብተ : ሰማይ : ወለኃይለ : ሰማያት ፤ ለሰማይ : ጭፍራ : ከዋክብት : ለነበሩ : ለደቂቀ : ሴት : የግዞት : ቤት : ሆናቸው ፤ ወከዋክብት : እለ : ያንኰረኵሩ : ዲበ : እሳት ፤

በእሳት : ውስጥ : ሰሚገለባበጡ ኮከቦችም : ይህ : የግዞት : ቤት ሆናቸው ፤

፴፰ ፤ ወእሉ : እሙንቱ : እለ : ኀለፉ : ትእዛዘ : እግዚአብሔር : እምቅድመ : ጽባሖሙ ፤

እነርሱም : በእውቀት : በደግነት : ፍጹም : ከመሆናቸው : አስቀድሞ ፤ እስመ : ኢመጽኡ : በጊዜሆሙ ፤

በጊዜያቸው : ጊዜ : አልመጡምና ፤ አንድም : በጊዜያቸው : ጊዜ : አልመጡምና : ምንም : ባይመጡ : ተምየሙ : ብለህ : ወደታች : እሠር ፤

፴፱ ፤ ወተምየሙ : ወአሠሮሙ : እስከ : ጊዜ : ተፍጻሜተ : ኃጢአቶሙ ፤ በኃጢአታቸው : የመጣባቸው : ፍዳ : እስኪፈጸምባቸው : ድረስ ተቆጥቶ : አጋዛቸው ፤

በዓመተ : ምሥጢር ፤

ዓቢይ : ዓለም ፡ መንግሥተ : ሰማይ ፣ ለጻድቃን : ዓቢይ : ዓለም ፤ ገሃነመ : እሳት : ለኃጥአን : የሚሰጥበት : ነውና : ምሥጢር : አለው ፤

፵፤ ፤ ወይቤለኒ : ዑርኤል : በዝየሰ : ተደሚሮሙ : መላእክት : ምስለ : አንስት ፤

ዑራኤልም : በዚህ : በቦታው ፤ አንድም : በግብሩ : ደቂቀ : ሴት : ከሴቶች : ጋራ : አንድ : ሁነው ፤ ይቀውሙ : መናፍስቲሆሙ ፤

ነፍሶቻቸው : በገሃነም : ይኖራሉ : አሰ ፤

፵፩ ፤ ወብዙኀ : አርአያ : ከዊኖሙ : አርኩሰምሙ : ለሰብእ ፤

በብዙ : ወገን : አብነት : ሁነው ሰዎችን : አረከሷቸው ፤ አንድም አርኩሰምሙ : ብዙኀ : አርአያ : ብዙኀ : ብሎ : ይገጥማል ፤ አብነት : ሁነው : ፈጽመው : አረከሷቸው ፤ ወያስሕትዎሙ : ለሰብእ : ከመ : ይሡዑ : ለአጋንንት : ከመ : አማልክት ፤ ምዕመናን : ለሥላሴ : እንዲሠዉ : እነሱም : ለጣዖታት : ሠዉ ፤

እስመ : በዕለት : ዓባይ : ዙኔ : በዘይ ትኬነኑ : እስከ : ይትፈጸሙ : በዕለት : ዓባይ ፤

ታላቅ : በሆነች : ቀን : እስኪያጠፉአቸው : ድረስ : ጽኑ : ፍርድ : በሚፈረድባት : በዕለተ : ምጽአት : በሚፈረድባቸው : ገንዘብ : ይፈረድባቸዋልና : ይሠዋሉ ፤

፵፪ ፤ ወእንስትያሆሙኒ : እስሐቶን : መላእክተ : ሰማይ : ከመ : ሰላማውያት : ይከውና ፤

ሴቶቻቸውም : ክፍ : ባለ : ማዕረግ : የነበሩ : የሴትን : ልጆች : አስተው : እንደ : ደኅና : ይሆናሉ ፤ ሴት : መነኵሲት : ወንዱን : መነኵሴ : አስታ : ደኅንኛ : እንድትመስል ፤

ጉባኤ

፩ ፤ ወአነ : ሄኖክ : ርኢኩ : አር
ዐያ : ባሕቲትየ ፤
እኔ : ሄኖክ : የብቻዬን : ነገር
የብቻዬን : ምሥጢር : አየሁ ፤
አንድም : ሳይናበብ : ብቻዬን :
ምሥጢር : አየሁ ፤
አጽናፈ : ኵሉ ፤
በጽንፈ : ምድር : ያለውን : ሁሉ :
አየሁ ፤
ወአልቦ : ዘርእየ እምሰብእ ዘከመ :
አነ : ርኢኩ :
እኔ : እንዳየሁት : ያየ : የለም
አለ ፤ ራእዩ : ልዩ : ልዩ : ነውና ፤
አንድም : እርሱ : ያየውንም :
ያየ : የለምና ::

ምዕራፍ ፪

፩ ፤ ወዝንቱ : ውእቱ : አስማቲ
ሆሙ : ለአለ : ይተግሁ : ቅዱሳን :
መላእክት ፤
ለቅዳሴ ፤ ለተልዕኮ ፤ ለተራድኦ
የሚተጉ ፤ የቅዱሳን : መላእክት :
ስማቸው : ይህ : ነው ፤
፪ ፤ ዑራኤል : ፩ዱ : እመላእክት
ቅዱሳን ፤
ከከበሩ : ከመላእክት : አንዱ :
ዑራኤል : ነው ፤ ዑራኤል : ማለት :
ብርሃነ : እግዚአብሔር : ማለት :
ነው ፤
እስመ : ዘረዓም : ወዘረዓድ ፤
በመብረቅ : በነጐድጓድ : የተሾመ :
ነውና ፤
፫ ፤ ሩፋኤል : ፩ዱ : እመላእክት :
ቅዱሳን : ዘመናፍስተ : ሰብእ ፤
ከሊቃነ : መላእክት : አንዱ :
ሩፋኤል : ነው ፤ ሩፋኤል : ማለት :
ፈውሰ : እግዚአብሔር : ማለት :
ነው ፤ ዘመናፍስተ : ሰብእ : አለው :
በሰው : ነፍላት : ወይም : በሰው :
ቍስል : የተሾመ ፤
፬ ፤ ራጉኤል : አሐዱ : እመላእክት :
ቅዱሳን ፤
ከከበሩ : መላእክት : አንዱ :
ራጉኤል : ነው ፤ ራጉኤል : ማለት :
ራእየ : እግዚአብሔር ማለት :
ነው ፤
ዘይትቤቀሉ : ለዓለም ፤
ይህን : ዓለም : የሚያሳልፍ ፤
ወለብርሃናት ፤
ፀሐይን : ጨረቃን : የሚያሳልፍ ፤
ፍጡራንንስ : በፍጡር : እጅ : አያ
ሳልፋቸውም : ብሎ : ዲያብሎስን :
የሚበቀል ፤
ወሎብርሃናት ፤
አጋንንትን : የሚበቀል ፤ እስመ
ለሊሁ : ሰይጣን : ይትሜሰል :
ከመ : መልአከ : ብርሃን : እንዲል[፩] ፤
አንድም : ህየንተ : ብርሃናት : ቢል :
ሰለ : ጸድቃን : ዲያብሎስን : የሚ
በቀል ፤
፭ ፤ ሚካኤል : አሐዱ : እመላእክት :
ቅዱሳን ፤
ከሊቃነ : መላእክት : አንዱ : ቅዱስ :
ሚካኤል : ነው ፤ ሚካኤል : ማለት :
መሐሪ : ወመስተሣህል : ማለት :
ነው ፤ ዕፁብ : ነገርም : ይለዋል ፤

፩ ፣ ፪ኛ ቆሮ. ፲፩ ፥ ፲፬

እስመ : በዲበ : ሠናይቱ : ለሰብእ : ተአዛዚ : ዲበ : ሕዝብ ።
ጌታ : በሚያደርገው : ቸርነት : ላይ፣ ለሰብእ ፣ ለሕዝብ : አንድ : ወገን : ነው ። ለሰው : ታዛዥ : ነውና ። ለሰው : በሚያደርገው : በጎነቱ : ላይ : ለሕዝቡ : ታዛዥ : ነውና ።

፮ ። ሠረቃኤል : አሐዱ : እመላእክት : ቅዳሳን ።
ከከበሩ : የከበረ : ከመላእክት : አንዱ : ሠረቃኤል : ነው ። የዚህ : ስሙ : አልተተረጐመም ። አን ድም : ፀዋሬ : ስም : ሠረቀ : በሥጋ : ወሀቤ : አእምሮ : ማለት : ነው ።
ዘዲበ : መናፍስተ : ዕጓለ : እመ ሕያው : ዘመናፍስተ፡ የኀጥኡ ፣
አእምሮ : ባጡ : ሰዎች : ላይ የተሾመ ።

፯ ። ገብርኤል : አሐዱ : እመላእክት : ቅዱሳን ።
ከከበሩ : ከሊቃን : መላእክት : አንዱ : ገብርኤል : ነው ። ገብርኤል፡ ማለት : አምላክ : ወሰብእ : ማለት : ነው ።
ዘዲበ : አኪስት ።
አጋንንት : መርዝ : እንዳይበጠ ብጡ : በምንጭ : ላይ : የተሾመ ።
አክይስት : ቢል : በእባቦች : ላይ : የተሾመ ።
ወዘዲበ : ገነት ፣
በገነት : ባሉ : ጻድቃን : የተሾመ ፣
በገነት : ያሉ : ጻድቃንስ : በእደ እግዚአብሔር : ነው : እንጂ : በእደ : መልአክ : አይጠበቁም : ብሎ : በገነት : ባሉ : ዕፀው ።
አዕዋፍ : የተሾመ ።
ወዘኪሩቤል ።
በኪሩቤል : ላይ : የተሾመ ።
ሚካኤል : በነገደ : ሱራፌል : እንደ : ተሾመ ። ገብርኤልም : የተሾመ : በነገደ : ኪሩቤል : ነውና ።

፰ ። ወያድኩ : እስከ : መካን : ኀበ : አልቦ : ዘይትገበር ።
ሥራ : ወደማይሠራበት : ቦታ ድረስ : ዞርኩ ።
ወርኢኩ : በሀየ፡ ግብረ : ግሩመ ።
በዚያም : የሚያስፈራ : ሥራን : አየሁ ፣
ኢሰማየ : ልዑለ : ወኢምድረ፡ ሡርርተ : አላ : መካነ : በድው : ዘድልው : ወግሩም ።
ጽንዕተ : ሲል : ነው ። ምድረ፡በዳ : ነው : እንጂ : ወደ : ላይ : ሰማይ : ወደታች : ጽንዕት : ምድር : የለም ።
ስነ : ፍጥረት ነው ። አንድም : መካነ : ኃጥአን : ነው ። ላገኛ ቸው : መከራ : ፍጻሜ : እንደሌ ለው : ለማጠየቅ ።

፱ ። ወበሀየ : ርኢኩ : ፮ተ : ከዋክ ብተ : ሰማይ : እሥራን : በላዕሌሁ : ኅቡረ ።
በዚያም : ቦታ : እንደ : ታላላቅ፡ ተራሮች : አንድ : ሁነው : በሱ የተጋዙ : ሰባት : የሰማይ : ኮከቦ ችን : አየሁ ። ደቂቀ : ሴት፡ናቸው ።

በፍጹም : ተናግሮ : ሰባት : አለ ። ከዋክብት : አላቸው : በጥንተ : ግብራቸው : ነው ።

ከመ : አድባር : ዓበይት : ወከመ : ዘአሳት : እንዘ : ይነድዱ ።

አሳት : እንደ : ተያያዛቸው : እንደ : ታላላቆች : ተራሮች : የሚነዱ : ደቂቀ : ሴትን : ከዚያ : አንድነት : ሁነው : አየሁ ።

፲ ። ይእተ : ጊዜ : ዕቡ : በእንተ ዓይ : ኃጢአት : ተአሥሩ ።

ያን : ጊዜም : በምን : ኃጢአት : ታሥረው : ተግዘዋል ?

ወበእንተ : ምንት : ዝየ : ተገድፉ ።

በምንስ : ኃጢአታቸው : በዚህ ወድቀዋል ? አልሁ ።

፲፩ ። ወይቤለኒ : ዑርኤል : ፩ዱ : እመላእክት : ቅዱሳን : ዘምስሌየ : ውእቱ : ወይመርሐኒ ።

ከእኔ : ጋራ : ያለ : ወደ : ወደደ ውም : ሥራ : የሚመራኝ : ከስ በሩ : ከመላእክት : አንዱ : ዑራኤ ልም : እንዲህ : አለኝ ።

ወይቤ : ሄኖክ : በእንተ : መኑ : ትሴአል : ወበእንተ : መኑ : ትጤ ይቅ : ወትጽሕቅ ።

ሄኖክ : ስለማን : ትጠይቃለህ ? ስለማንስ : ልትረዳ : ትተጋለህ ? አለኝ ።

እምከዋከብት : አለ : የኃልፉ : ትእ ዛዘ : እግዚአብሔር ።

ከደቂቀ : ሴት : አንድ : ሳይቀሩ : በእግዚአብሔር : ትእዛዝ : የተ ጋዙ ። አንድም : ትእዛዘ : እግዚአብሔርን : ያሰፉ : ናቸው ።

፲፪ ። እሱ : እሙንቱ : መላእክት አለ : ኃሰፉ : ትእዛዘ : እግዚአብሔር ልዑል ።

እኒህ : ከፍ : ያለ : የእግዚአብሔርን ትእዛዝ : ያፈረሱ : የሴት : ልጆች : ናቸው ።

ወተአሥሩ : በዝየ : እስከ : ይትፈጸም ትእልፊተ : ዓለም : ጕልቈ : መዋዕለ ኃጢአቶሙ ።

የኃጢአታቸው : ዘመን : ቍጥር የሚሆን : የዚህ : ዓለም : ቍጥር : እስኪፈጸም : ድረስ : ተግዘዋል ።

፲፫ ። ወእምዝየ : ሖርኩ : ካልዓ መካነ : እምዝ : ዘይጌርም ።

ከዚያም : ከዚህ : ቦታ : ወደሚያ ስፈራ : ወደሌላ : ቦታ : ሔድኹ ።

፲፬ ። ወርኢኩ : ግብረ : ግሩመ ።

በዚያም : የሚያስፈራ : ሥራ : አየሁ ።

እሳት : ዓቢይ : በሀየ : ዘይነድድ : ወያንበለብል ።

በዚያም : ቦታ : ፈጽሞ : የሚቃ ጠል : ታላቅ : ቋያ : አለ ።

ወሞሰርት : ቦቱ ።

መጋዝ : አለበት ።

ወወሰኑ : እስከ : ቀላይ : ፍጹም ።

ጥርሱ : በምልዓት : ፍጹም : እስከሆነ : እስከ : ውቅያኖስ : ነው ። አንድም : ወሞሰርት : ሰይፍ : አለ ። ወሰኑ : ጫፉ : በምልዓት : ፍጹም : እስከ : ሆነ : እስከ : ውቅያኖስ : ነው ።

፲፫ ፤ አዕማደ : እሳት : ዓበይት : ዘያወርድዎሙ ፤
ሥላሴ : መላእክት : ወደሲኦል ወደገሃነም : የሚያወርዷቸው : ደቂቀ : ሴት: አስበት ፤
ወኢአምጣኖ ፤
የወርዱን : ቁመቱን ፤
ወኢዕበዮ ፤
ስፋቱን ፤
ኢክህልኩ : ነጽሮ ፤
ማየት : አልቻልኹም ፤
ወስዕንኩ : ነጽሮ : ዓይኑ ፤
መልክዑ : ሲል : ነው ፤ መልኩንም : ማየት : አልቻልኹም ፤ አንድም : ወነጽሮ ፤ ማየት : አልቻልኹም ፣ ዓይኑ : ምንድር : ነው ?
፲፬ ፤ ውእተ : ጊዜ : እቤ : እፎ : ግሩም : ዝንቱ : መካን : ወሕማም ለነጽሮ ፤
ያን : ጊዜም : ይህ : ቦታ : እንዴት : የሚያስፈራ : ነው ፤ ሲያዩትም : ደዌ : ነው : አልኩ ፤
፲፭ ፤ ውእተ : ጊዜ : አውሥአኒ ዑርኤል : ፩ዱ : እመላእክት : ቅዱሳን : ዘምስሌየ : ሀለወ ፣
ያን : ጊዜም : ከእኔ : ጋራ : ያለ : ከከበሩ : ከመላእክት : አንዱ : ዑራኤል : መለሰልኝ ፤
፲፮ ፤ ወአውሥአኒ : ወይቤለኒ : ሄኖክ : ምንት : ውእቱ : ፍርሃትከ : ከመዝ ፣
ሄኖክ : እንደዚህ : አድርገህ : መፍራትህ : ምንድር : ነው?
ወድንጋፄከ : በእንተዝ : ግሩም : መካን : ወቅድመ : ገጹ : ለዝ : ሕማም ፤
ስለዚህ : ስለሚያስፈራው : ቦታስ ? በዚህ : መከራ : ፊት : ይህን : ያህል : መደንገጥህ : ለምንድር ነው ?
፲፱ ፤ ወይቤለኒ : ዝ : መካን : ቤተ : ሞቅሖሙ : ለመላእክት : ወበህየ ይትአገዙ : እስከ : ለዓለም ፤
ይህም : ቦታ : ለደቂቀ : ሴት : የግዞት : ቦታቸው : ነው ፤ በዚያም : ቦታ : እስከ : ዘለዓለም ድረስ : ይጋዛሉ ፤
፳ ፤ ወእምህየ : ሖርኩ : ካልዐ መካነ ፤
ከዚያም : ወደ : ሌላ : ቦታ : ሄድኹ ፣
ወአርአየኒ : በምዕራብ : ደብረ : ዓቢየ ወነዋኑ ፣
በምዕራብም : ረጅምና : ታላቅ: የሆነ : ተራራን : አሳየኝ ፣
ወኩሉሐ : ጽኑዐ ፤
የጸና : ዐለትንም : አሳየኝ ፤
፳፩ ፤ ወፀውቱ : መካናት: ሠናያት፣
በአጠገቡ : ያማማሩ : አራት : ቦታዎች : አሉ ፤ ሠናያት : መካነ : ኃጥአንን : በመካነ : ጻድቃን : አስጠግቶ : ሠናያት : አለ ፤
ወበውስቴቱ : ዘቦቱ : ዕሙቅ : ወርሒብ ፤
በውስጡ : ሰፊነት : ጥልቅነት አለ ፤ አንድም : ወበውስቴቱ : ወበጥቃሁ : ሲል : ነው ፤ በመ

ካነ : ጻድቃን : አጠገብ : ያለ : መካነ : ኃጥአን : ዕሙቅ : ጥልቅ: ነው ። ወርሒብ ። ሰፊ: ነው ። ወልሙጽ : ጥቀ : ከመ : ልሙጽ : ዘያንኰረኵር ።

እንደልዝብ : ደንጊያ : የሚያዳ ልጥ : ነው ።

ወዕሙቅ : ወጽልመት : ለነጽሮ ። ለማየት : ጥልቅ : ጨለማ : ነው ።

፰ ። ውእተ : ጊዜ : አውሥአኒ ሩፋኤል : ፩ዱ : እመላእክት : ቅዱ ሳን : ዘሀለወ : ምስሌየ ።

ያንጊዜም : ከነበሩ : መላእክት ከእኔ : ጋራ : ያለ : አንዱ : ሩፋ ኤል : መለሰልኝ ።

፱ ። ወይቤለኒ : እላ : መካናት : ሠናያት : ከመ : ይትጋብኡ : ዲቤሆን : መናፍስቲሆሙ : ለምውታን : ሎሙ : እሎንቱ : ተፈጥሩ ።

ተፈጥራ : ሲል : ነው ። እላና : እሎንቱ : አንድ : ወገን ። ተድላ : ደስታ : የተመላባቸው : እኒህ : ቦታዎች : በምግባር : በሃይማ ኖት : ፍጹማን : የሆኑ : ጻድቃን : ይገቡባቸው : ዘንድ : ተፈጠሩላ ቸው ።

ወዝየ : ያስተጋብኡ : ነፍሳተ : ውሉደ ሰብእ ።

ሥላሴ ። መላእክት : የደጋግ : ሰዎች : ነፍሶችን : ከዚህ : ይሰበ ሰቡ ዘንድ : ይሰበስባሉ ።

፲ ። ወእሉንተ : መካናተ : ኀበ ያነብርዎሙ : ገብሩ ።

እነርሱ : የሚያኖሩባቸውን : ቦታዎች : በነው : ቦታ : ለጻድቃን : እንደ ተፈጠረ : ክፉውም : ቦታ ለኃጥአን : ተፈጠረ ።

እስከ : ዕለተ : ኵነኔሆሙ ። እስኪፈረድባቸው ።

ወእስከ : አመ : ዕድሜሆሙ ። እስከ : ዘመናቸው : ድረስ ።

፲፩ ። ወዕድሜ : ዓቢይ : ውእቱ ። ዘመኑም : ብዙ : ነውና ።

እስከ : አመ : ኵነኔ : ዓቢይ : በላዕ ሌሆሙ ።

ፍጹም : ፍርድ : በእነርሱ : ላይ : እስኪደረግ : ዘመኑም : ብዙ : ነው ።

፲፪ ። ወርኢኩ : መናፍስተ : ውሉደ : ሰብእ : እንዘ : ምውታን : ውእቶሙ ። የደጋግ : ሰዎች : ልጆች : ነፍሶ ችንም : አየሁ ።

ወእንዘ : ምውታን : ውእቶሙ : ወቃ ሎሙ : ይበጽሕ : እስከ : ሰማይ : ወይሰክ ።

የጻድቃን : ነፍሶች : ምውታን : ሁነው : ሳሉ : ቃላቸው : እስከ ሰማይ : ሲደርስ : ኃጥአንን : ሲከሰ : ሲያጣላ አየሁ ።

፲፫ ። ውእተ : ጊዜ : ተስእልክዎ : ለሩፋኤል : ዘሀሎ : ምስሌየ ።

ያንጊዜም : ከእኔ : ጋራ : ያለ : ሩፋኤልን : ጠየቅሁት

ወእቤሎ : ዝ : መንፈስ : ዘመኑ : ውእቱ ።

ይህ : የማን : ነፍስ : ነው? አልኩት ፤
ዘከመዝ : ቃሉ : ይበጽሕ : እስከ : ሰማይ : ወይሰኪ፤
ቃሉ : እስከ : ሰማይ : የሚደርስ ፣ የሚከስ ፣ የሚያጣላ : የማን :ነፍስ : ነው ? አልኩት፤
ፀ፯ ፤ ወአውሥኣኒ : ወይቤለኒ : እንዘ : ይብል : ዝንቱ : መንፈስ : ውእቱ : ዘይወጽእ : እምአቤል ዘቀተሎ : ቃየል : እጊሁ ፤
ይህ : ነፍስ ፣ ወንድሙ : ቃየል በግፍ : ከገደለው : ከአቤል : የተለየ : ነፍስ : ነው : አለኝ ፤
ወይሰኪ : ኪያሁ : እስከ : አመ : ይት ጎጕሉ : ዘርዑ : እምገጸ : ምድር፤
ልጁ : (ዘሩ) : ከዚህ : ዓለም : እስኪ : ጠፋ : ድረስ ፤
ወእምዘርአ : ሰብእ : ይማስን : ዘርዑ፤
ልጁ : ዘሩ : ከሰው : ልጅ : ተለ ይቶ : እስኪጠፋ : ድረስ : ነው ፤
ፀ፰ ፤ ወውእተ : ጊዜ : ተሰእልክም በእንቲአሁ ፤
በቃየል :የሚፈረድበትን ፤
ወበእንተ : ኵነኔ : ኵሉ ፤
በኃጥአን : የሚፈረድባቸውን ፤
አንድም : ለአቤል : የሚፈረድ ለትን ፤ አንድም : ለጻድቃን : የሚፈረድላቸውን : ጠየቅሁት ፤
ወአቤ : በእንተ : ምንት : ተፈልጠ : ፩ዱ : እም፩ዱ ፤
የጻድቃን : ቦታ : ከኃጥአን ፤ የኃ ጥአን : ቦታ : ከጻድቃን : ስለምን : ተለየ ? ብዬ : ጠየቅሁት ::
፸ ፤ ወአውሥኣኒ : ወይቤለኒ : እሱንቱ : ፫ቱ : ተገብሩ : ከመ : ይፍ ልጡ : መንፈሶሙ : ለሙታን ፤
የጻድቃንን : ነፍስ : ከኃጥአን : ይለዩ : ዘንድ : እነዚህ : ሦስቱ ቦታዎች : ተፈጠሩ ፤
ወከመዝ : ተፈልጡ : መንፈሶሙ : ለጻድቃን ፤
የጻድቃን : ቦታቸው : እንደ : ተለየ : ነፍሳቸውም : ተለየ ፤
ዝውእቱ : ነቅዓ : ማይ : ዘበላዕሌሁ ብርሃን ፤
ብርሃን : በላዩ : ላይ : ያለበት ነቅዓ : ማይ : የውኃ : ምንጭ ፤
ይህ : ነው ፤ አንድም : ብርሃን ጌታ : ያደረበት : የክብር : የልጅ ነት : ቦታ : ይህ : ነው ፤
፸፩ ፤ በከመ : ከማሁ : ተፈጥረ : ለኃጥአን : ሶበ : ይመውቱ : ወይት ቀበሩ : ውስተ : ምድር ፤
አሁን : እንደተናገርሁት : ለጻድ ቃን : በጎው : ቦታ : እንደተፈጠረ: ለኃጥአንም : በዚህ : ዓለም : ሙተው : በተቀበሩ : ጊዜ : ሊኖ ሩበት : ክፉው :ቦታ : ተፈጠረ፤
፸፪ ፤ ወኵነኔ : ኢኮነ : በላዕ ሌሆሙ : በሕይወቶሙ ፤
በሕይወት : ሳሉ : አልተፈረደባ ቸውም : ነበረና ፤
፸፫ ፤ ወበዝየ: ይትፈለጣ : ነፍሳቲ ሆሙ : ዲበ : ዛቲ : ዓባይ : ፃዕር : እስከ : አመ : ዓባይ : ዕለት : እንተ : ኵነኔ፤

እስከ : ዕለተ : ምጽአት : ድረስ ይህችን : ጭንቅ : መከራ : ሊቀ በሉ : ኃጥአን : ከጻድቃን : በዚህ : ቦታ : ይለያሉ ፤

ወመቅሠፍት : ወዓፅር : ለእለ : ይረግሙ : እስከ : ለዓለም : ወበቀል ለነፍሶሙ ፤

እግዚአብሔርን : ለሚክዱ ፣ ሰውን : ለሚሳደቡ ፣ ይህች : ጭንቅ : መከራ : ለዘለዓለሙ : አለችባቸው ፤ ለነፍ ሳቸውም : በቀል : አለባት ፤

፲፩ ፤ ወበሆየ : የአሥሮሙ : እስከ ለዓለም : ወእመኒ : ውእቱ : እምቅ ድመ : ዓለም ፤

ምንም : እንኳ : ከዓለም : ጀምሮ : ቢሆን : እስከ : ዘለዓለሙ : አሥሮ : ያግዛቸዋል ፤ ዓለም : ገሃነመ : እሳት : ለኃጥአን ፣ ዓቢይ : ዓለም : መንግሥተ : ሰማይ : ለጻድቃን : ከመስጠቱ : አስቀድሞ : ቢሆን : በዚህ : ይታሠራሉ ፤

፲፪ ፤ ወከመዝ : ተፈልጠ : ለነፍ ሶሙ : ለእለ : ይሰክዩ : ወእለ : ያሬእዩ : በእንተ : ኅጕለት : አመ : ተቀትሉ በመዋዕለ : ኃጥአን ፤

የኃጥአን : ቦታ : እንደተለየ : በኃጥ አን : ወራት : በሞቱ : ጊዜ : የጥፋ ታቸውን : ነገር : የሚያሳዩ : ኃጥ አንን : ለሚከሱ ፤ እግዚአብሔርን : ለሚለምኑ : ለጻድቃን : ነፍስ : ቦታ : ተለየ ፤

፲፫ ፤ ወከመዝ : ተፈጥሩ : ለነፍ ሶሙ : ለሰብእ : እኩያን : እለ : ኢኮኑ : ጻድቃነ ፤ አላ : ኅጥአነ : እለ : ፍጹማነ : አበሳ ፣

በኃጢአት : ፍጹማን : የሆኑ ፣ ኃጥ አንን : እንጂ : ጻድቃን : ላይደሉ : የክፉዎች : ሰዎች : ነፍስም : ለጻድቃን : እንደተለየ : ቦታ : ተለየ ፤

ወምስለ : አባሲያን : ይከውኑ : ከማሆሙ ፤

እኩሌቶቹ : ኃጥአን : እንደ : እኩሌቶቹ : ኃጥአን : ይሆናሉ ፤ አንድም : እኩሌቶቹ : ኃጥአን : ከእኩሌቶቹ : ኃጥአን : ጋራ : ይፈረድባቸዋል ፤ አንድም : ኃጥ አን : ከአጋንንት : ጋራ : ይፈረድ ባቸዋል ፤

፲፬ ፤ ወነፍሶሙሰ : ኢትትቀተል : በዕለተ : ኩነኔ ፤

በፍርድ ቀን : መከራ : ስትቀ በል : ትኖራለች : እንጂ : ነፍሳ ቸው : ግን : አትሞትም ፤ አን ድም : ሰውነታቸው : ሳትነሣ : ፈርሳ : በስብሳ : አትቀርም ፣

ወኢይትነሥኡ : እምዝየ ፣

ትንሣኤያቸው : ዘለኃሣር : ስለ ሆነ : ኢይትነሥኡ : አለ ፤ አንድም : ከገሃነም : አይወጡም ፤

፲፭ ፤ ውእተ : ጊዜ : ባረክዎ : ለእግዚአ : ስብሐት ፤

ያን : ጊዜም : የክብር : ባለ ቤት : ጌታዬን : አመሰገንሁት ፤

ወእቤ : ቡሩክ : ውእቱ : እግዚእየ : እግዚአ : ስብሐት ፣ ወጽድቅ ፣ ዘኵሉ : ይመልክ : እስከ : ለዓለም ፤

እስከ : ዘለዓለሙ : ድረስ : ሁሉን : የሚችል : የክብርና : የጽድቅ : ጌታዬም : የተመሰገነ : ነው : አልሁ ፤

ወጽድቅ : ቢል ፤ ፈታሒ : በጽ
ድቅ : ጌታዬ : ቡሩክ : ነው :
አልሁ ፤
፴፱ ፤ ወእምህየ : ሖርኩ : ካልአ :
መካነ : መንገለ : ዓረብ : እስከ :
አጽናፈ : ምድር ፤
ከዚያም : እስከ : ምድር : ዳርቻ
ድረስ : በምዕራብ : ወዳለ :
ወደሌላ : ቦታ : ሄድኹ ፤
፵ ፤ ወርኢኩ : አሳተ : ዘይነድድ :
ወይረውፅ : እንዘ : ኢያዐርፍ ፤
ሳያርፍ : እየሮጠ : የሚነድድ :
አሳትንም : አየሁ : ፀሐይን :
ነው ፤
ወኢይነትግ : እምሩፀቱ : መዓልተ :
ወሌሊተ ፤
በመዓልትም : በሌሊትም : ከመ
ሄዱ : ሳያቋርጥ : ሳያርፍ :
አየሁ ፤
አላ : ከማሁ : ክመ ፤
በመዓልትም : በሌሊትም : መቸም :
መች : ይሄዳል : እንጂ ፤
፵፩ ፤ ወተሰዕልኩ : እንዘ : እብል :
ዝንቱ : ምንት : ውእቱ : ዘአልቦ
ዕረፍት ፤
ይህ : ዕረፍት : የሌለው : ምን
ድነው ? ብዬ : ጠየቅሁ ፤
፵፪ ፤ ውእተ : ጊዜ : አውሥአኒ
ራጉኤል : ፩ዱ : እመላእክት : ቅዱሳን
ዘሀሉ : ምስሌየ ፤
ያን : ጊዜ : ከእኔ : ጋራ : ያለ :
ከከበሩ : ከመላእክት : አንዱ :
ራጉኤል : መለሰልኝ ፤
ወይቤለኒ : ዝንቱ : ዘርኢክ : ሩጸቶ :
ዘመንገለ : ዓረብ : አሳት : ዘይነድድ፤
ወደምዕራብ : ሲኼድ : ያየኸው
የሚያበራ : ይህ : አሳት ፤
ውእቱ : ዞሱ : ብርሃናተ : ሰማይ ፤
ይኸውም : ፀሐይ : ጨረቃ :
ከዋክብት : ናቸው ፤ አንዱን :
ፀሐይን : ከጠየቀ : ዘንድ :
ከዚህ : አያይዞ : ሁሉንም :
ነገረው ::

ምዕራፍ ፯ ፤
ጉባኤ

፩ ፤ ወእምህየ : ሖርኩ : ካልአ :
መካነ : ምድር ፤
ይህን : ራእይ : ካየሁበት : ወደ
ሌላ : ቦታ : ሄድኹ : አለ ፤
ወአርአየኒ : ደብረ : አሳት : ዘያን
በሰብል : መዓልተ : ወሌሊተ ፤
በመዓልትም : በሌሊትም : የሚ
ያበራ : የዕንቊ : ተራራ : አየሁ ፤
አንድም : የሚያበራ : ዕንቊ : ያለ
በትን : ተራራ : አየሁ ፤
፪ ፤ ወሖርኩ : መንገሌሁ : ወርኢኩ
፯ተ : አድባረ : ክቡራነ ፤
የከበሩ : ሰባት : የዕንቊ : ተራ
ሮችን ፤ አንድም : ዕንቊ : ያለባ
ቸው : ተራሮችን : አየሁ ፤
፫ ፤ ወዞሱ : ፩ዱ : እምነ : ፩ዱ :
እንዘ : ይትዌለጥ ፤
አንዱ : ካንዱ : በመልክም : በብ
ርሃንም : ይለወጣል ፤

ወእዕባነ : ክቡራን ። ወሠናያነ ። ያማሩና : የከበሩ : ድንጋዮችንም: አየሁ ።

ወከሉ : ክቡር ።

ሁሉም : ጽሩያን : ናቸው።

፬ ። ወስቡሕ : ራእዮሙ ።

መልካቸው : የበራ : ብሩህ : ነው ።

ወሠናይ : ገጾሙ :

አካላቸው : ጽሩይ : ነው ፣ ፊታቸውም : ያማረ : ነው ።

ወሠለስቱ : መንገለ : ጽባሕ ።

ሦስቱ : በምሥራቅ : ናቸው ።

ወጽኑዓን : ፩ዱ : ዲበ : ፩ዱ ።

አንዱን : ካየሁት : በኋላ : ያየሁት : አንዱም : አንዱም : ጽኑዓን : ናቸው ። አንድም : ጽዑናን : ቢል : አንዱ : ከአንዱ : ጋራ: የተያያዙ : የተደራረቡ : ናቸው ።

፭ ። ወሠለስቱ : መንገለ : ሰሜን : ፩ዱ : ዲበ : ፩ዱ : ጽኑዓን ።

ሦስቱም : በሰሜን : በኩል : ናቸው : አንዱን: ካየሁ : በኋላ : ያየሁት : አንዱም : አንዱም : ጽኑዓን : ናቸው ። አንድም: ጽዑናን : ቢል : አንዱ : ከአንዱ : ጋራ : እንደ : ጣት : የተያያዙ : ናቸው ።

ወቁላት : ዕሙቃት : ወጠዋያት ።

ጠማማ : ጥልቅ : የሆኑ : ቁላምች : አሉ : አለ ፣ በኃጢአት : በክህደት : ፍጹማን : የሆኑ : የሚኖሩባት : ብሔረ : አሕዛብ : አለ ።

አሐቲ : ለአሐቲ : ኢይትቃረባ ።

አሐቲ : ወአሐቲ : እንደማለት ። አንዲቱና : አንዲቱ : አይቀራረቡም ። አንድም : ኢትቀርባ : ቢል : አንዲቱ : አንዲቱን : አትቀርባትም ። አሕዛብ : በግብርም : በኃጢአትም : አይቀራረቡም : ሥራቸው : ልዩ : ልዩ: ነውና ።

፮ ። ወሳብዕ : ደብር : ማእከሎሙ ለእሉንቱ ።

በመካከላቸው ፯ተኛ : ተራራ : አለ ።

ወኮኖሙስ : ይትማሰሉ : ኵሎሙ : ከመ : መንበረ : አትራኖስ ።

ቁመታቸውም : እንደ : አፍርንጂ : ወምበር : የተካከለ : የተመሳሰለ : ነው ። ለጊዜው : እንዲህ : ያለ : አሳይቶታል ፣ ለኋላው : ምሳሌ : ነው ። መጀመሪያ : ያየው : ተራራ ፣ ገነት : ናት ። በዚያ : ያሉ : አዳምና : ሔዋን : ናቸው ። ሁለተኛ : ያየው : ተራራ : ደብር : ቅዱስ : ነው ። በዚያም : ያሉ : ደቂቀ : ሴት : ናቸው ። ሦስተኛ : ያየው : ተራራ : ሐመረ : ኖኅ : ናት ። በዚያ : ያሉት : ኖኅ : ከነልጆቹ : ናቸው ። አራተኛ : ያየው : ተራራ : ደብረ : ሲና : ነው ፣ በዚያ : ያሉ : ሙሴ : አሮን : ናቸው ። አምስተኛ : ያየው : ደብረ : ዘይት : ነው ። በዚያ : ያሉ : ዳዊት : ሰሎሞን : ናቸው ።

ስድስተኛ : ያየው :ደብረ : ታቦር : ነው ፣ በዚያ : ያሉ : ባርቅ : ዲቦራ : ናቸው ፤ ሰባተኛ : ያየው : ቀራንዮ : ነው ፣ በዚያ : ያሉ : ጌታ : ሐዋርያት : ናቸው ፤ ሳብዕ : ያለው : ደብረ : ሲና : ነው ፣ አሁን : ስተራራው : እንዲህ :ያለ ፣ ማእከል : አለው ፤ በምሥራቅ : ያሉ : ገነት ፣ ደብር : ቅዱስ ፣ ሐመረ : ኖኅ : ናቸው ፤ በምዕራብ ያሉ : ደብረ : ዘይት ፤ ደብረ : ታቦር ፣ ቀራንዮ ፣ ናቸው ፣ መካከሉ : ደብረ : ሲና : ነው ፣

፮ ፤ ወየዐውድዎ : ዕፀወ : መዓዛ ፣ መዓዛ : ያላቸው : እንጨቶች : ከበውታል ፣ ማለት : ሕገጋቱ : ከበውታል ፣

ወሀሎ : ውስቴቶሙ : ዕፅ : አልቦ : ግሙራ : አመ : ዜነወኒ : ወኢአሐዱ እምውስቴቶሙ ፤

በመካከላቸውም : አንድ : እንጨት : አለ ፣ በሽተተኝም : ጊዜ : ከእነርሳቸው : አንዱ : ስንኪ : እንደ : እርሱ : የሸተተኝ : የለም ፤ አንድም : ኢታምልክ : በመካከላቸው : አለ ፣ ከሕግጋቱም : ሁሉ : ጸጋ : ክብር : በመስጠት : ኢታምልክን : የሚመስለው : የለም ::

፯ ፤ ወባዕዳንሂ : ዘከማሁ : ኢኮነ : ዘይምዕዝ እምኵሉ : መዓዛ ፤

ኢኮነም : ካለ : ባዕድሂ ፣ ባዕዳ ንሂም : ካለ : ኢኮኑ : ባለ : በቀና : ነበር ፤ በሸተተኝ : ጊዜ መዓዛ : ካላቸው : ዕፀው : እንደ እርሱ : የሚሸት : የለም ፣ ማለት : ጸጋ : ክብር : ካላቸው :ሕገጋት : ጸጋ : ክብር : በማሰጠት : እንደ : ኢታምልክ : ያለ : የለም ፤

፰ ፤ ወቁጽዖሂ : ወጽጌሁ ፣ ወዕፀ : ኢይጸመሂ : ለዓለም ፣

ቅጠሉ ፣ አበባው ፣ እንጨቱ ፣ ለዘለዓለም : አይጠወልግም ፣ ማለት : በኢታምልክ : የሚገኘው : ጸጋ ፣ ክብር ፣ አይጠፋም ፣ ማለት : ነው ፤

፱ ፤ ወፍሬሁኒ : ሠናይ ፣ ፍሬውም : ብዙ : ነው ፤

ወፍሬሁሰ : ከመ : አስካለ : በቀልት ፤ ፍሬውም : እንደ : ዘንባባ : ፍሬ : ንብብር : ነው ፣ ማለት : በኢታምልክ : የሚገኘው : ክብር : ብዙ : ነው ፤ በፊት : ለማየት : ደስ : የሚያሰኝ : ነው ፤ ማለት : ኢታምልክ : በዓይነ : ልቡና : ለማየት : ደስ :የሚያሰኝ : ነው ፤

፲ ፤ ወውእተ : ጊዜ : ዕቤ : ነዋ : ዝንቱ : ሠናይ : ዕፅ : ወሠናይ : ለርእይ : ወአዳም : ቄጽሉ : ወፍሬሁኒ : ሞገስ : ጥቀ : ለርእየ : ገጽ ፤

ያን : ጊዜም : ይህ እንጨት : እነሆ ያማረ : ነው ፤ ቅጠሉ : ጽፍቅ : ነው ፣ ፍሬው : ንብብር : ሊያዩትም : ፊጽሞ : የተወደደ ነው : አልሁ ፤

፲፩ ፤ ወውእተ : ጊዜ : አውሥአኒ ፤ ሚካኤል : አሐዱ : እመላእክት :

ቅዱሳን : ወክቡራን : ዘምስሌየ : ሀሎ ወውእቱ : ዘዲቤሆሙ ፣

ያን : ጊዜ : ከእኔ : ጋራ : ያለ በላያቸው : የተሾመ ፣ ከሊቃነ : መላእክት : አንዱ : ቅዱስ : ሚካኤል : መለሰልኝ ፤

፲፫ ፤ ወይቤለኒ : ሄኖክ : ምንተ : ትሴአል : በእንተ : መዓዛሁ : ለዝ : ዕፅ : ወትጤይቅ : ከመ : ታእምር፤ ሄኖክ : የዚህን : የእንጨት : ሽታ : ነገር : ለምን : ትጠይቃለህ? ልታ ውቅስ : ለምን : ትመረምራ ለህ? አለኝ ፤ ማለት : የዚህን : የኢታምልክን : ነገር : ልታወቅ ትወዳለህ ? አለኝ፤

፲፬ ፤ ውእተ : ጊዜ : አውሣእክም : አነ : ሄኖክ : እንዘ : እብል : በእንተ ዙሉ : እፈቅድ : አእምር : ወፈድፋ ደሰ : በእንተዝ : ዕፅ ፤

ያን : ጊዜ : እኔ : ሄኖክ : እንዲህ : ብዬ : መለስኩለት ፣ ማወቅስ : የዕፀውን : ነገር : ሁሉ : ላውቅ : እወዳለሁ ፣ ይልቁንም : የዚህን : የዕፅ : ነገር : ላውቅ : እወዳለሁ ፣ ማለት : ማወቅስ : የሕገጋቱን : ነገር : ሁሉ : ላውቅ : እወዳለሁ፣ ይልቁንም : የኢታምልክን : ነገር : ላውቅ : እወዳለሁ ፤

፲፭ ፤ ወአውሥአኒ : እንዘ : ይብል : ዝንቱ : ደብር : ዘርኢከ : ነዋህ : ዘር እሱ : ይመስል : መንበር፡ ለእግዚእ : መንበሩ : ውእቱ : ኀበ : ይነብር : ቅዱስ : ወዓቢይ : እግዚእ : ስብሐት፡ ንጉሥ : ዘለዓለም : ሶበ : ይወርድ : የሐውጻ : ለምድር : በሠናይ ፤

እርሱም : እንዲህ : ብሎ : መለ ሰልኝ ፤ ራሱ : የእግዚአብሔርን : ዙፋን : የሚመስል : ልዑል : ሁኖ : ያየኸው : ይህችን : ዓለም : በበጎ : ነገር ሊጐበኝ : በመጣ : ጊዜ : የሚቀመጥበት : የእግዚአ ብሔር : ዙፋን : ነው ፤ ማለት : ራሱ : የእግዚአብሔርን :ዙፋን ፤ የሚመስል : ልዑል : ሁኖ : ያየኸው :በበጎ : ነገር : በዘፈቀደ ተገልጾ : ሕግ : ሠርቶ :በተገለጸ ጊዜ : የሚቀመጥባት : ደብረ : ሲና : ናት ፤

፲፮ ፤ ወዝንቱኒ : ዕፀ : መዓዛ : ሠናይ ፣ ወኢይጼዱ : ዘሥጋ : አልቦ : ሥልጣን ከመ : ይግሥሦ ፤

ለዝንቱኒ : ሲል : ነው ፤ ይህን ንም ፣ ዕፅ : ከሥጋዊ : ከደማዊ : አንዱም : አንዱም : ይነካው : ዘንድ : ሥልጣን : የለውም : ማለት ፤

አስክ : አመ ዓቢይ : ኵነኔ : አመ : ይትቤቀል : ዙሉ : ወይትፈጸም : አስክ : ለዓለም፤

ፍጹም : ፍዳ : በኃጥአን ፤ ፍጹም : ክብር : በጻድቃን : በተፈጸመ : ጊዜ : ኃጥአንን : በተበቀለ : ጊዜ : ፍጹም : ቍርጥ : ፍርድ : አስኪደርስ : ይነካው : ዘንድ : ሥልጣን : የለውም ፤ በዘመነ : ብሉይ :

እለ : ጼሩጻይጻን : እለ : አንጥ
ያኮስ ፤ በዘመነ : ሐዲስ : እለ :
መክስምያናስ : እለ : ዲዮቅል
ጥያኖስ : ተነሡ ፤ አላጠፉትም ፤
፲፯ ፤ ዝኩ : ለጻድቃን : ወለትሑ
ታን : ይትወሀብ : እምፍሬ : ዚአሁ ፤
ከፍሬው : ትሑታን : ለሆኑ :
ለጻድቃን : ይሰጣል ፤ ማለት :
በኢታምልክ ፡ የሚገኘው ክብር :
ለጻድቃን : ይሰጣል ፤
ወይትወሀብ : ለጎሩያነ : ሕይወት ፡
በምግባር : በሃይማኖት : ለተመ
ረጡ : በኢታምልክ : የሚገኘው
ክብር : ይሰጣል ፤
፲፰ ፤ መንገለ : መስዕ : ይተከል :
ውስተ : መካን : ቅዱስ : መንገለ :
ቤቱ : ለእግዚእ : ንጉሥ : ዘለዓለም ፤
የዘላለም : ንጉሥ : ወደሚሆን :
በደጊቱ : ማደሪያ : በዘላለማዊው :
ንጉሥ : በጌታ : ቤት : አንፃር :
በመስዕ : በኩል : በቅዱስ : ቦታ :
ባለ : በክቡር ቦታ : ይተካከላል ፤
በመካን : ቅዱስ : ደብረ : ሲና :
መንገለ : መስዕ ፤ ደብረ : ሲና :
በመስዕ በኩል : ነውና : መንገለ :
ቤቱ : አለ ፤ ደብረ : ሲና : በቤተ :
መቅደስ : አንፃር : ነውና ፤ ይህን :
በበሉ : ጊዜ ፤
፲፱ ፤ ውስተ : ጊዜ : ይትፈሥሑ :
በፍሥሓ : ወይትሐሠዩ ፤
ያን : ጊዜ : ፈጽመው : ደስ :
ይላቸዋል ፤
፳ ፤ ውስተ : ቅዱስ : ያበውኡ :
ሎቱ : መዓዛ : በበአዕፅምቲሆሙ ፤
በየወገናቸው : ወደ : ከበረ : ቦታ :
ሽቱን : ያቀርቡለታል ፤
ወሕይወተ ፡ ብዙኅ : የሐይዉ : በዲበ
ምድር : በከመ : ሐይዉ : አበዊከ ፤
አባቶችህ : ብዙ : ዘመን : እን
ደኖሩ ፤ እነሱም : በዚህ : ዓለም :
ብዙ : ዘመን : ይኖራሉ ፤ ደስ :
ይላቸዋል ፤ ማለት : ኢታምልክን :
ባወቁ : ጊዜ : ደስ : ይላቸዋል ፤
፳፩ ፤ ሁሉ : መዓዛ : ያቀርቡ
ለታል : ማለት : እሥራኤል : ሁሉ :
ኢታምልክን : ያከብሩታል ፤ ያገ
ኙታል ፤ ቀድሞ : ይህን : የበሉ :
ሰዎች : በሕይወት : እንደኖሩ :
እንግዲህም : ከዚህ : ዕፅ : የበሉ :
ሰዎች : በሕይወት : ይኖራሉ ፤
ማለት : ኢታምልክን : በሕገ :
ልቡና : አምነው : የኖሩ : ሰዎች :
በሕይወት : እንዲኖሩ ፤ ኋላም ፤
የተነሡ : ሰዎች : ኢታምልክን :
እየጠበቁ : በሕይወት : ይኖራሉ ፤
ይህን : በሚበሉበት : ዘመን :
ሕማም : መከራ : የለባቸውም ፤
ማለት : ኢታምልክን : በሚጠ
ብቁበት : ዘመን : ሕማመ : ሥጋ ፤
ሕማመ : ነፍስ ፤ ኀዘነ : ሥጋ :
ኀዘነ : ነፍስ ፤ ድካመ : ሥጋ :
ድካመ : ነፍስ : የለባቸውም ፤
፳፪ ፤ ወበመዋዕሊሆሙ : ኃዘን :
ወሕማም : ወፃማ : ወመቅሠፍት :
ኢይገሥሦሙ ፤

በዘመናቸው : መከራና : ኃዘን ፤ መቅሠፍትና : ድካምም አያገኛ ቸውም፤ (አይዳስሳቸውም) ፤
ፀሄ ፤ ውእተ : ጊዜ : ባረክም ፡ ለእግዚአ : ስብሐት : ንጉሥ : ዘለ ዓለም ፤
እንደዚህም ፡አድርጎ : ፈጥሮ : ሰጥ ቷቸዋልና ፡የዘለዓለም : ንጉሥ : የሚሆን : የክብር : ባለቤት : ጌታን : አመሰገንሁት አለ ፤
አስመ : አስተዳለወ : ከመዝ ለሰብእ ጻድቃን ወከመዝ : ፈጠረ ፤
እንዲህ : አድርጎ : ወዳጆቹ : ስለሆኑ : ሰዎች ፡ኢታምልክን : አዘጋጅቷልና ፤
ወይቤ : የሀብሙ ፤
ይህን : ዕፅ : ይሰጣቸው ፡ዘንድ : አሏልና ፣ ማለት ፡በኢታምልክ : የሚገኘውን : ሥርዓት : ያስተም ሯቸው ፡ዘንድ : አስተምሯቸው: ብሎ : አሏልና ፡አመሰገንሁት ፤
አንድም : ሳብዕ : ደብር : ቀራን ዮን : ማዕከል : አለው ፤ በም ሥራቅ : ያሉ : ገነት ፤ ደብር: ቅዱስ ፤ ሐመረ : ኖኅ ፡ ናቸው፤
ወደ : ምዕራብ : ያሉ : ደብረ : ሲና ፤ ደብረ : ዘይት ፤ ደብረ : ታቦር : ናቸው ፤ መዓዛ : ያላቸው : ዕፀው : ከበውታል : ማለት ፡የጻድቃን : የሰማዕታት: መከራ : ከበውታል ፤ መከራ: የሚቀበሉ : ጌታን : አብነት : እያደረጉ ፡ነውና ፤ በውስጣቸው: ከእርሳቸው ፡መዓዛ : የሚበልጥ: ዕፅ : አለ : ማለት ፡ጸጋ : ክብር : በማሰጠት : ከሰማዕታት : የሚበ ልጥ ፡የጌታ : መስቀል : አለ፤
በሸተተ : ጊዜ : በመዓዛ : የሚመ ሰለው : የለም : ማለት : ጸጋ : ክብር : በማሰጠት : የሚመስ ለው ፡የለም ፤ ጻድቃን ፡ሰማዕ ታት : እንከበርበት : ብለው : ነው ፤ እሱ : ግን: እከብር : አይል ፡ክቡር ፤ እጸድቅ ፡አይል : ጻድቅ : ነውና ፤ ቅጠሉ ፣ አበ ባው፣ እንጨቱ ፡አይጠወልግም ፣ ማለት ፡በመስቀል ፡የሚገኘው : ክብር ፡አይጠፋም ፣ ፍሬው ፡ንብ ብር ፡ነው ፤ ማለት ፡በመስቀል ፡ የሚገኘው : ክብር: ብዙ ፡ነው ፤ ለፊት ፡ደስ : ያሰኛል ፡ማለት ፡ መስቀል : ለዓይን : ሕሊና : ደስ ፡ያሰኛል፣ ያንጊዜ ፡ከሊቃነ : መላእክት : አንዱ : ቅዱስ : ሚካኤል ፡የዚህን ፡ዕፅን ፡ነገር : ልታውቅ: ትወዳለህ ? ማለት : የጌታን : መከራ : ልታውቅ : ትወዳለህ ? አለኝ ፤ ማወቅስ : ሁሉንም : ላውቅ : እወዳለሁ ፣ ይልቁንም: የዚህን : ዕፅ: ነገር ላውቅ : እወዳለሁ ፤ ማለት : ማወቅስ : የጻድቃን ፡ የሰማዕታ ትን ፡መከራ ፡ላውቅ ፡እወዳለሁ፤ ይልቁንም ፡ የጌታን ፡ መስቀል : ላውቅ : እወዳለሁ ፤ ራሱ : የጌታን : ዙፋን : የሚመስለው ፡

ረጅም : ሁኖ : ያየኸው : በበጎ : ነገር : ሊጐበኛት : በመጣ : ጊዜ : የሚቀመጥበት : የእግዚአብሔር ዙፋን : ነው ፤ ማለት : ይህን : ዓለም : ለማዳን : ሥጋውን : ቈርሶ ፣ ደሙን : አፍስሶ : ባዳ ነው : ጊዜ : የሚሰቀልበት : መስቀል : ነው ፤ ከሥጋዊ : ከደ ማዊ : አንዱም : አንዱም : ይነካው : ዘንድ : ሥልጣን : የለውም ፤ ማለት : ጸጋ : ክብር የሚያሰጥ : መስቀልን : ማጥፋት : የሚቻለው : የለም ፤ አይሁድ : ሁለት : ጊዜ ፤ ሮማውያን : አንድ : ጊዜ ፤ የቀበሩት : መስቀል : ተነሥቶባቸዋልና : ለተመረጡ : ሰዎች : ከዚህ : ዕንጨት : ፍሬ : ይሰጣል ፤ ማለት : በምግባር : በሃ ይማኖት : ለተመረጡ : ሰዎች : በመስቀል : ከሚገኘው : ክብር : ይሰጣል : ማለት : ነው ፤ በመ ስዕ : በኩል : ይተከላል : ማለት : ወደመስዕ : ፊቱን : መልሰው : ጌታን : ሰቅለውታልና : በመካን : ቅዱስ : ማለት : በቀራንዮ ፤ መንገለ : ቤቱ : ማለት : ቀራ ንዮ : በቤተ : መቅደስ : አጠ ገብ : ነውና ፤ ከዚህ : ዕፅ : በበሉ : ጊዜ : ደስ : ይላቸዋል ፤ ማለት : ይህን : የመስቀልን : ፀጋ : ክብር : ባገኙ : ጊዜ : ፊጽመው : ደስ ይላቸዋል ፤ ዕፀው : ሁሉ : በየወገናቸው : መዓዛ : ያገቡለታል : ማለት ፤ ምዕመናን : ለመስቀል : ምስጋና : ያገቡለታል ፤ መስቀል : ኃይልነ ፤ መስቀል : ጽንዕነ ፣ የማይለው : የለምና ፤ ከዚህ : ዕፅ : የበሉ : ሰዎች : በሕይወት እንዲኖሩ ፣ እንግዲህም : የሚነሱ : ሰዎች ከዚህ : ዕፅ : እየበሉ : በሕይወት : ይኖራሉ ፤ ማለት : በመስቀል : ተሰቅሎ : ያድነናል ብለው : አምነው : በሕይወት : እንደኖሩ : ዛሬም : በመስቀል : ተሰቅሎ : አድኖናል : ብለው : አምነው : በሕይወት :ይኖራሉ ፤ በዘመናቸው : ይህን : በበሉበት ወራት : ኀዘን : ድካም ፣ የለም ፣ ማለት ፤ መስቀልን : ባመኑበት : ወራት : ኀዘነ : ሥጋ ፣ ኃዘነ : ነፍስ ፣ ድካመ : ሥጋ : ድካመ : ነፍስ : የለባቸውም ፤ ይህን : ዕፅ : አዘጋጅቶላቸዋልና ፤ ይህን ዕፅ : ይሰጧቸው : ዘንድ : አዝዟልና ፣ ማለት ፤ መስቀልን : አዘጋጅቶላቸዋልና ፣ በመስቀል : የሚገኘውን : ጸጋ : ክብር : ጻድቃን : ለሆኑ : ሰዎች : አዘጋጅቷልና : አመሰገንሁት ፤ አንድም : ስድስቱ ተራሮች : ማለት : በስድስቱ : ቃላተ : ወንጌል : ያመኑ : ናቸው ፤ ሳብዕ : ደብር : እመቤታችን ፣ ዕፀው :

ሁሉ : ከበውታል ፤ ማለት : የጻድቃን : ንጽሕና : ቅድስና : ድንግልና : ከበውታል : ሲል : ነው ፤ በውስጣቸው : ያለውን: አንዱን : የሚመስለው ፡ የለም፤ ማለት : የእመቤታችንን : ንጽሕና : ድንግልና : ከጻድቃን : ንጽሕና : ድንግልና : የሚመስለው : የለም ፤ ቅጠሉ :አበባው: አይጠወልግም : ማለት : በእመቤታችን: ድንግልና : የሚገኘው : ክብር : አይጠፋም ፤ ፍሬው : እንደ : ዘምባባ: ንብብር ነው ፤ ማለት : በእመቤታችን : ድንግልና : የሚገኘው : ክብር : ብዙ : ነው ፤ ለዓይን : ደስ : የሚያሰኝ : ነው ፤ ማለት : በእመቤታችን : ድንግልና : የሚገኘው : ክብር : ለዓይነ : ልቡና ደስ : የሚያሰኝ : ነው ፤ ያንጊዜ ከሲቃነ : መላእክት : አንዱ : ቅዱስ : ሚካኤል : የዚህን : የዕፅ : ነገር : ልታውቅ : ትወዳለህ ? አለኝ : ማለት : የእመቤታችንን : ንጽሕናዋን : ድንግልናዋን : ልታውቅ : ትወዳለህ ? አለኝ ፤ ማወቅስ : መላውን : ዕፅ : ላውቅ : እወዳለሁ : ይልቁንም : የዚህን : ዕፅ : ነገር ላውቅ : እወዳለሁ ፤ ማለት : ማወቅስ : የጻድቃንንም : ንጽሕና ፣ ድንግልና : ላውቅ : እወዳለሁ ፤ ይልቁንም : የእመቤታችንን : ድንግልና ፣ ንጽሕና : ላውቅ : እወዳለሁ : አልሁት ፤ ራሱ : የእግዚአብሔርን : ዙፋን : የሚመስል : ሪጅም : ሁኖ : የም ታየው : ዓለምን : በበጎ : ነገር : ይጐበኘው ; ዘንድ : በመጣ : ጊዜ : የሚቀመጥበት : ዙፋኑ : ነው ፣ ማለት : ሰው : ሁኖ : ሥጋ : ለብሶ : በመጣ : ጊዜ : የሚያ ድርባት : እመቤታችን : ናት ፤ ከሥጋዊ ፣ ከደማዊ : አንዱም : አንዱም : ይህን : ዕፅ : ይነካው : ዘንድ : ሥልጣን : የለውም ፤ ማለት : የእመቤታችንን : ንጽ ሕና ፣ ድንግልና : የሚያጠፋው የለም ፤ አይሁድ : እሩቅ : ብእሲ : ወልደ : ዮሴፍ : ብለውታል ፤ አንጢዲቁማርያጦስ : ያጡስያው ያን : ሲያውያን : ዘውእቶሙ : ፀረ : ማርያም : ይላቸዋል ፤ ባንድ : ስም : ሲሆን : አንጢዲ ቁማርያጦስ : ዘውእቱ : ፀረ : ማርያም : እምድኅረ ወለደቶ : ለእግዚእነ : ተደመረት ምስለ : ዮሴፍ : ብሏል ፤ ነገር : ግን : ማጥፋት : አልተቻላቸውም : ይለዋል ፤ የዚህ : ዕፅ : ፍሬ : ለተመረጡ : ሰዎች : ይሰጣል: ማለት : በእመቤታችን : ድንግ ልና : የሚገኘው : ክብር : በም ግባር : በሃይማኖት : ለተመረጡ : ሰዎች : ይሰጣል : ማለት : ነው ፤

መስዕ ፣ መካን ፣ ቅዱስ ፣ መን
ገለ : ቤቱ : ያለው : አንድ :
ወገን : ነው ፤ በእመቤታችን :
ጌታ : ያድራል : ማለት : ነው ፤
ይህን : በበሉ : ጊዜ : ፈጽመው :
ደስ : ይላቸዋል ፤ ማለት :
በእመቤታችን : ድንግልና : የሚ
ገኘውን : ክብር : ባገኙ : ጊዜ
ፈጽመው : ሳይጠራጠሩ : ደስ
ይላቸዋል ፤ ዕፀው : ሁሉ :
በየወገናቸው : መዓዛቸውን :
ይሰጣሉ ፤ ማለት : ምዕመናን :
ሁሉ : ለእመቤታችን : ምስጋና
ያቀርባሉ ፤ ሰአሊ : ለነ : ቅድስት ፤
ሳትባል : አትውልም : አታድር
ምና : ነው ፤ ከዚህ : ዕፅ : የበሉ :
ሰዎች : በሕይወት : እንደኖሩ :
ዛሬም : የሚነሡ : ሰዎች : ቢበሉ :
በሕይወት : ይኖራሉ ፤ ማለት :
ከእመቤታችን : ተወልዶ : ያድነ
ናል : ብለው : አምነው : ያሉ :
በሕይወት : እንደኖሩ ፣ ኋላም :
ከእመቤታችን : ተወልዶ : አድኖ
ናል : ብለው : አምነው : በሕይ
ወት :ይኖራሉ ፤ ይህን : ዕፅ :
የበላ : ሰው : ኀዘን : የለበትም ፤
ማለት : በእመቤታችን : ባመ
ኑባት : ወራት : ኀዘነ : ሥጋ ፣
ኀዘነ : ነፍስ ፣ ድካመ : ሥጋ ፣
ድካመ : ነፍስ : የለባቸውም ፤
የእመቤታችንን : ድንግልና :
አዘጋጅቷልና ፤ በድንግልና :
የሚገኘውን : ክብር : ጸድቃን :
ለሆኑ : ሰዎች : ይሰጧቸው :
ዘንድ : ስጧቸው : ብሎ : አሏልና :
አመሰገንኩት ፤ መጀመሪያ : ወየ
ዐውድም : ብለህ : ንባቡን :
ተርጉም ፤ ኋላ : ሦስት ጊዜ :
እያወረድህ : መልስ ፤
ፀ፫ ፤ ወአምህየ : ሖርኩ : ማዕከለ:
ምድር : ወርኢኩ : መካነ : ቡሩክ፤
ሰባቱን : ተራራ ካየሁ : በኋላ ፣
በሴም : ዕጣ : ሁሉ : ሄድሁ ፤
ወጥሉለ ፤
እንተ : ታውጎዝ : ሀሊበ :
ወመዓረ : የተባለች ፤
ዘቡቱ : አዕፀቅ: ዘይነብር : ወይሠርዕ
እምዕፅ : ዘተመትረ ፣
ተቈርጦ : የተተከለ ፣ የለመለመ :
እንጨት : ያለበት ፤ አንድም : ከነ
ቢያት : በትንቢት : የተወለዱ ፤
በመንፈስ : ቅዱስ : የከበሩ ፤
ሐዋርያት : ያሉባት : ኢየሩሳ
ሌምን : አየሁ ፤
ፀ፬ ፤ ወበህየ : ርኢኩ : ደብረ :
ቅዱስ ፤
በዚያ : ቦታ : ቤተ : መቅደስን :
አየሁ ፣
ወመትሕተ : ደብር : ማይ : ዘመን
ገለ : ጽባሑ ፤
ከተራራው : በታች : ከወደ : ምሥ
ራቁ : ውኃ : ይፈስሳል : አለ ፤
ከነቢያት : የሚገኝ : ትምህርት
በቤተ : መቅደስ : ይነገራል ፤
ወውጎዘቱ : መንገለ : ሰሜን ፤
አፈሳሰሱ : ወደ : ሰሜን : ነው ፤
የሚነገረው : ለፀኤል : ነው ፤

፮፩ ፤ ወርኢኩ : መንገለ : ጽባሕ : ካልአ : ደብረ : ዘይነውኅ : እምዝ ፤ በምሥራቅም : በኩል : ከዚህ የረዘመ : ተራራ : ደብረ : ታቦርን : አየሁ ፤

፮፪ ፤ ወማዕከሉሙ : ቁላ : ዕሙቅ ፤ ብሔረ : አሕዛብን : አየሁ ፤ ወአልቦ : ራሕብ ፤ ወርድ : ስፋት : የለውም ፤ አንድም : ስፍሐ : አዕምሮ : የለውም ፤ ስፉሐ : አእምሮም ይላል : ሳያናብብ ፤ ወላቲኒ : የሐውር : ማይ : መንገለ ደብር ፤ እመንገለ : ደብር : እንደማለት ከተራራው : ውኃ : ይፈስላታል፤ ከነቢያት : የሚገኝ : ትምህርት ለብሔረ : አሕዛብ : ይነገራል ፤

፮፫ ፤ ወመንገለ : ዓረቡ : ለዝ : ካልእ : ደብር ፤ በዚህ : ተራራ : በግራው : በኩል : ካልእ : አርሞንኤም : አለ ፤ ወይቴሐቶ : ሎቱ : ወአልቦ : ኑኅ ወቁላ : ታሕተ : ማዕከሉሙ ፤ በዚህ : በሁለተኛው : ተራራ : ምዕራብ : አጠገብ : ከእርሱ : የሚያንስ :ተራራ : አርሞንኤም አለ : (ያንሰዋል) :

፮፬ ፤ ወካልኣት : ቁላት : ዕሙቃት ፤ ጥልቅ : የሆኑ : ቁላዎች : አሉ፤ አንድም : በመካከላቸው : በክህደት : በኃጢአት : ፍጹማን : የሆኑ : አሕዛብ : የሚኖሩባቸው ብሔረ : አሕዛብ : አሉ ፤ ወይቡሳት ፤ ይቡሳን : አእምሮ : አሕዛብ : የሚኖሩባት ፤ መንገለ : ጽንፈ : ፫ቲሆሙ ፤ በሦስቱ : ተራራ : አጠገብ : በሐውርተ : አሕዛብ : አሉ ፤ ሳብዕ : ደብር : ያለውን : የተረጐሙ : እንደሆን : ሌላ : አመጣ : ብሎ : እንዲህ : እንደ ተረጐምነው : ብሎ : መዜድ ፣ ሳብዕን : ሳይተረጕሙ : የመጡ : እንደሆን : ሦስቱን : ተናገራቸው ፤ ቤተ : መቅደስ ፣ ደብረ : ታቦር ፣ አርሞንኤም : አራቱን : በቃል : ደብረ : ዘይት ፣ ቀራንዮ : እስክንድርያ ፣ ደብረ : ቊስቋም ፤ አንድም : ማዕከለ : ምድር : ወደ ኢየሩሳሌም : ሄድሁ ፤ መካነ : ቡሩክ : ቤተ : መቅደስ : ደብር : ቅዱስ ፣ ደብረ : ዘይት ፣ ካለአ : ደብረ ፣ ደብረ : ታቦር ለዝ : ደብር : ካልእ : አርሞንኤም : ነው ፤ የቀረው : ትርጓሜ : አይለወጥም : ወመንገለ :ፀ፫ቲሆሙ : ፬፫ቲሆሙ : እንደማለት ፤ በቤተ : መቅደስ ፣ በደብረ:ዘይት : በደብረ : ታቦር : በአርሞንኤም :አጠገብ : በሐውርተ : አሕዛብ : አሉ : ፮ቱን : ለመምላት ፫ቱን በቃል ያመጣል ፤ ደብረ : ሲና :

ቀራንዮ : ከእስክንድርያና : ከደብረ : ቊስቋም : አንዱን : አግብቶ : ነው ፤

፹፱ ፤ ወኵሉ : ቊላት : ዕሙቃት ፤ ጥልቅ : የሆኑ ፤

ወአልቦን : ራሕብ ፤

ስፋት : የሌላቸው : ቊላዎች : አሉ ፤ አንድም : በክህደት : በኃጢአት : ፍጹማን : የሆኑ ፤ ስፍሐ : አእምሮ : የሌላቸው : አሕዛብ : የሚኖሩባቸው : ብሐውርተ : አሕዛብ : አሉ ፤

እምኵሎሕ : ጽኑዕ ፤

ከጽኑ : ድንጋይ : የተፈጠረ : ጽኑ : ድንጋይ : አለ ፤ አንድም ስነ : ፍጥረት ፤ አንድም : ከጽኑዓነ : ልቡና : አሕዛብ : የተወለዱ : አሕዛብ : አሉ ፤

፺ ፤ ወዕፅ : ይተከል : በላዕሌሆን ፤ በእነርሱ : ላይ : ዕፅ : ይተከላል : አለ ፤ ሕግ : ይሠራባቸዋል ፤

ወአንከርኩ : በእንተ : ኵሎሕ ፤

ስለ : ዐለቱ : አደነቅሁ ፤

ወአንከርኩ : በእንተ : ቊላት ፤

ስለ : ሽለቆዎችም : አደነቅሁ ፤

አለ ፤ የአሕዛብን : ነገር : አደነቅሁ ፤

ስለ : እስራኤልም : አደነቅሁ ፤

ወጥቀ : አንከርኩ ፤

ይልቁን : የአሕዛብን : ነገር : አደነቅሁ : አለ ፤ በብሒረ : አሕዛብ : እንግር : መካነ : ኃጥአንን ፤ በብሒረ : እስራኤል : እንግር : መካነ : ጻድቃንን ያሳየዋልና ፤

፺፩ ፤ ውእተ : ጊዜ : እቤ : በእንተ ምንት : ዛቲ : ምድር : ቡርክት : ወኵለንታሃ : ዕፀው : ምልእት ፤

ዕፀውን : ሁለመናዋ : የተመላች : ይህች : ቡርክት : ምድር : ለምን : ተፈጠረች ? መንግሥተ : ሰማያትን ፤

፺፪ ፤ ወዛ : ቊላ : ርግምት : ማዕከሉሙ ፤

ይህች : ርግምት : ቦታስ : በመካከላቸው : ለምን : ተፈጠረች ? ገሃነመ : እሳትን ፤

፺፫ ፤ ውእተ : ጊዜ : አውሥአኒ : ዑርኤል : አሐዱ : እመላእክት : ቅዱሳን : ዘሀሉ : ምስሌየ ፤

ያን : ጊዜም : ከኔ : ጋራ : ያለ ከከበሩ : ከመላእክት : አንዱ : ዑራኤል : መለሰልኝ ፤

ወይቤለኒ : ዛ : ቊላ : ርግምት : ለርጉማን : እስከ : ለዓለም ፤

እንዲህም : አለኝ ፤ ይህች : ርግምት : ቦታ : እስከ : ዘለዓለሙ : ሊኖሩባት : ለርጉማን : ኀጥአን : ተፈጠረች ፤

፺፬ ፤ ወዝየ : ይትጋብኡ : ኵሉመ እለ : ይብሉ : በአፋሆሙ : ላዕለ : እግዚአብሔር : ቃለ : ዘኢይደሉ ፤ በቃላቸው : በእግዚአብሔር : ላይ : የማይገባ : ነገርን : የሚናገሩ : ሰዎች : ሁሉ : በዚያ : ቦታ : ይሰበሰባሉ ፤

፺፭ ፤ ወበእንተ : ስብሐተ : ዚአሁ : ይትናገሩ : ዕፁባተ : ዝየ : ያስተጋብ

ዕፆሙ : ወዝየ : ምኵናኖሙ : በደ ኃሪ : መዋዕል ።
በጌትነቱ : ላይ : የማይገባ : ቃልን : የሚናገሩ : ሰዎችን : መላእክት ይሰበስቧቸዋል (አብነት : መላእ ክት ፣ ሥላሴ ፣ አጋንንት : ይሰ በስቧቸዋል) : ይላል ። በኋላኛው: ዘመንም : ፍርዳቸው : በዚያ : ይሆናል ።
፱፯ ። ወይከውን : ላዕሌሆሙ : አርአያ : ኵነኔ : ዘበጽድቅ : በቅድመ : ጻድቃን ።
በእውነት : የሚደረግ : የመቻያ ፍርድ : በጻድቃን : ፊት : ይደረ ግባቸዋል ።
፱፰ ። ወኵሉ : መዋዕለ : በዝየ ይባርክዎ : መሐርያን : ለእግዚአ ብሔት : ንጉሥ : ዘለዓለም ።
ለሰው : የሚያዝኑ ፣ የሚራሩ : ጻድቃን : ለዘላለም : የሚነግሥ : የክብር : ባለቤት : ጌታን : በዘ መኑ : ሁሉ : በዚያ : ያመሰ ግኑታል ።
፱፱ ። ወበመዋዕለ : ኵነኔሆሙ : ይባ ርክዎ : በምሕረቱ : በከመ : ከፈሎሙ ።
ይባርክዎ : በምሕረቱ : በከመ : ከፈሎሙ : በምሕረቱ : ብሎ : መግጠም : ነው ። በተፈረደላቸው : ወራት : በቸርነቱ : እንዳደላቸው : በቸርነቱ : ያመሰግኑታል :
፪፱ ። ውእተ : ጊዜ : አነኒ : ባረክዎ: ለእግዚአ : ስብሐት ።
እኔም : ያን : ጊዜ : የክብር : ባለቤት : ጌታን : አመሰገንሁት: ወሎቱ : ነገርኩ : ወዘከርኩ : በከመ ይደሉ : ለዕበዩ ።
ለገናንነቱም : እንደሚገባ : አድ ርጌ : ጌትነቱን: ተናገርሁለት : ስሙንም : ጠራሁ ::

ምዕራፍ ፷
ጉባኤ

፩ ። ወሐርኩ : መንገለ: ጽባሕ : ማዕከላ : ለደብረ : መድበራ ።
በምሥራቅ : በኩል : ባለ : ጽኑ በረሀ : ባለበት : ተራራ : መካ ከል : ሄድሁ ።
፪ ። ወርኢክዎ : ገዳመ : ባሕቲቶ ። ጽኑ : በረሀ : ሁኖ : አየሁት ። እንደ : አብረንታት ። በሰሜን : ያለ ሀገር : ነው :
፫ ። ወባሕቱ : ምሉዕ : ዕፅወ : እምነ : ዝንቱ : ዘርዕ ።
ነገር : ግን : ከዘር : የሚገኝ : ዕፀውን : (እንጨቶችን :) የተመላ : ነው ። ጥንቸን : ዘር : የሌለው : የለምና ። አንድም : ከጻድቃን : የተወለዱ : ጻድቃን : ያሉበትን መካነ : ጻድቃንን : አየሁ ።
፬ ። ወማይ : እምላዕሉ : ይፈለ ፍል : በላዕሉ ።
ከላይ : በላዩ : ላይ : ውሀ : ይመ ነጫል ።
እምላዕሉ : በላዕሉ : አለ ። የሚነ ገረው : ትምህርቱ : ሰማያዊ : ነው ። የሚነገረው : ርስት : ሰማ

ያዊ : ነውና ፤ የሚነገርላቸው : ሰማያውያን : ናቸውና ፤ ትምህ ርቱ : ከላይ : ይነገራል ፤

ያስተርኢ : አስራብ : ከመ : ብዙኅ : ዘይሰርብ ፤

ብዙኃ : ሊል : ነው ፤ ፈሳሽ : ብዙ : ሁኖ : ይፈስሳል : ትምህ ርቱ : ብዙ : ሆኖ : ይሰማል ፤

፷ ፤ ከመ : መንገለ : መስዕ : መንገለ : ዓረብ ፤

በመስዕ : በኩል : እንዲፈስስ : ወደ : ምዕራብም : ይፈስሳል ፤ አንድም : ትምህርቱ : እንደ : መስዕ : በምዕራብ ፤ ይነገራል ፤

ወእምኵለዜኒ : የዐርግ ፤

መስዕና : ምዕራብን : ሁለቱን : ተናግሮ : ነበርና : በአራት : መዓዝን : ይነገራል ፤

ወእምህየኒ : ማይ : ወጠል ፤

ማይ : ጠል : በቁሙ ፤ አንድም : ማይ : ትምህርት ፤ ጠል : ረድ ኤት : ይሰጣል ፤

፷፩ ፤ ወሖርኩ : ውስተ : መካን : ካልእ : እምነ : መድበራ : መንገለ : ጽባሑ : ለውእቱ : ደብር : ቀረብኩ ፤

ለዚህ : ተራራ : ምሥራቁ : ወደ : ሆነ ፤ ወደ : ምሥራቁ : በታ : ሄድሁ ፤

፷፪ ፤ ወበህየ : ርኢኩ : ዕፀወ : ዕጣኔ ፤ ሴቶች : ቀምመው : ተቀብተዋ ቸው : በወንዶች : መቻያ : የሚ ያመጡትን : ዕፀው : አየሁ ፤ አንድም : ሥርዓት : የተሠራባ ቸውን : ዕፀው : አየሁ ፤ አን ድም : ቢያፈርሷቸው : የሚያስ ፈርዱትን : ሕግጋት : አየሁ ፤ አንድም : ሕግ : የሚጠብቁ : ጻድቃንን : አየሁ ፤

ፈድፋደ : ቁሳቁስ : መዓዛ ፤

ብዙ : የሽታ : ቅመም : ያለባ ቸው ፤ አንድም : የሃይማኖት የምግባር : ቅመም : ያለባቸው ጻድቃንን : አየሁ ፤

ዘሰሂን : ወከርቤ ፤

የነጭ : ዕጣን : የከርቤ : መዓዛ የሚሆን ፤

ወዕፀውኒ : ኢይትማሰሉ ፤

እንጨቶችም : በመዓዛ : በመ ልክ : አይመሳሰሉም ፤ አንድም : ጻድቃን : በገድል : በትሩፋት : አይመሳሰሉም ፤

፷፫ ፤ ወላዕሌሁ : ላዕለ : እሉንቱ : ላዕለ : ደብረ : ጽባሕ : ወአኮ : ርጉዕ ፤ እነሱንም : ካየሁ : በኋላ : ወደ ምሥራቅ : ተራራ : ሄድሁ ፤ ፈጽሜም : የራቅሁ : አይደለሁም ፤

፷፬ ፤ ወርኢኩ : መካነ : ካልእ : ቄላተ ማይ : ከመ : ዘኢይትዋጸዕ ፤

ከመ : ቀሪ : ነው ፤ ላዕሌሁ : ላዕለ : እሉንቱ : ላዕለ : ደብር አንድ : ወገን : ነው ፤ ሩቅ : ሆኜ : ያይደለ : በተራራው : ላይ : የማይገታ : ውኃ : ያለበት : ቄላ : አየሁ ፤ አንድም : የማይ ፈጸም : ትምህርት : ያለበት : መካነ : ጻድቃንን : አየሁ ፤

፲ ፤ ወርኢኩ : ዕፀ : ሠናየ : ወመዓዛሁ : ከመ : ዘሰኢኖን ፤ መዓዛው : እንደ : ለውዝ : እንደ : ገውዝ : ያለ : እንጨትን : አየሁ ፤ አንድም : ምግባሩ ፣ ሃይማኖቱ : እንደ : አብርሃም : የሆነ : ጻድቅን : አየሁ ፤

፲፩ ፤ ወመንገለ : ክነፊሆሙ : ለቄላት : እሱንቱ : ርኢኩ : ቀናንሞስ : ዘመዓዛ ፤ ጽነፊሆሙ : ሲል : ነው ፤ በእነዚህ : ቄላምች : አጠገብ : ቀናንሞስ : ደርሰኔ : አየሁ ፤ አንድም : ምዑዘ : ምግባር : ወሃይማኖት : የሆነ : ጻድቅን : አየሁ ፤

፲፪ ፤ ወዲበ : እልክቱ : ቀረብኩ፡ ዘመንገለ : ጽባሕ ፤ እኒህን : ካየሁ : በኋላ : ወደ : ምሥራቅ : ቀረብሁ ፤ ወርኢኩ : ካልኦ : ደብረ : ዘዐ : ውስቴቱ : ዕፀው ፤ ዕፀው : ያሉበትን : ሌላ : ቦታን : አየሁ ፤ ስነ ፤ ፍጥረትን ፤ አንድም : ጻድቃን : ያሉበትን : ቦታ : አየሁ ፤ መካነ : ጻድቃን : ነው ፤

፲፫ ፤ ወይወጽእ : ማይ : እምኔሁ : ከመ : ነቁጥሮ : ዘሰሙ : ሣሪራ : ወከልበኒ ፤ ባንዱ : ልሳን : ሣሪራ : የሚባል : ጽሩይ : ውኃ : አየሁ ፣ በእርሱ ፤ ሲፈስስ : አየሁ ፤ ነቁጥሮ : ምዑዝ : ነው ፤ ምዑዝ : ውኃ : ሲፈስስ : አየሁ ፤ አንድም : በእርሱ : ያማረ : የተወደደ : ትምህርት : ሲነገር : ሰማሁ ፤ ወከልበኔ ፤ ልባንጃ : ሽቱ : ነው ፤ አንድም : ምዑዝ : ትምህርት : በእርሱ : ይነገራል ፤

፲፬ ፤ ወዲበ : ውእቱ : ደብር : ርኢኩ : ካልኦ : ደብረ ፤ በዚያም : ተራራ : ላይ : ሆኜ : ሌላ : ተራራን : አየሁ ፤ ወውስቴቱ : ዕፀው : ዘአልዎ ፤ በውስጡም : ዋግራ : የሚባሉ : እንጨቶች : አሉበት ፤ ዋግራ : ሽቱ : ነው ፤ አንድም : ጽኑ : ነው ፤ በምግባር : በሃይማኖት : የጸኑ : ጻድቃን : አሉበት ፤

፲፭ ፤ ወእልክቱ : ዕፀው : ምሉዓን : ዘከመ : ከርካዕ : ዘጽኑዕ ፤ እነዚህ : እንጨቶች : እንደፅኑ እንጨት : እንደ : ሎሚ : ያለ ሽቱ : የተመሉ : ናቸው ፤ አንድም : እሊህ : ጻድቃን : እንደ አብርሃም : በምግባር : በሃይማኖት : የጸኑ : ናቸው ፤ ወሶበ : ይነሥእም : ለውእቱ : ፍሬ : ይጌይስ : እምኵሉ : አፈው ፤ የዚህን : ፍሬ : ባነሡት ፣ በያዙት : ጊዜ : ከሽቱ : ሁሉ : ይበልጣል ፤ አንዱ : ጻድቅ : ካንዱ : ጻድቅ : ይበልጣል ፤

፲፮ ፤ ወእምድኅረ : እሉ : አፈው : ለመስዕ : እዝ : እኔጽር : መልዕልተ አድባር ፤

እሊህን : ሽቱዎች : ካየሁ : በኋላ : ወደመስዕ : ስመለከት ፤ ፲፯ ፤ ወርኢኩ : ፯ተ : አድባረ : ምሉዓነ : ሰንበልት : ቅድው ፤ ያማረ : ልባንጃ : ሽቱ : የተመሉ : ሰባት : ተራራዎችን : አየሁ ፤ ወዕፀወ : መዓዛ : ወቀናንሞስ ፤ ወጥጥሬ ፤ ደርሰኒ : ሽቱ ፣ ጥሩ : ሽታ : ያላቸው : እንጨቶችንም : አየሁ ፤ ጥጥሬ : የሚባል ፡ ሽቱ : የተመ ላባቸው : ሰባት : ተራራዎችን : አየሁ ፤ አንድም : ምዑዛነ : ምግባር : ወሃይማኖት : የሚሆኑ : ጻድቃን : የተመሉባት : መካነ : ጻድቃንን : አየሁ ፤ ፲፰ ፤ ወእምህየ : ሖርኩ : መልዕ ልተ : ርእሶሙ : ለእልክቱ : አድባር ፡ እንዘ : ርጉቅ : ውእቱ : ለጽባሕ ፤ ሖርኩ : ለጽባሕ : ሲል : ነው ፤ በዚህ : በተራሮች : ራስ : ላይ ሩቅ : ሁኜ : ሳለሁ ፣ ወደምሥ ራቅ : ሄድሁ ፤ ርጉቅ : የወርድ : የቁመት : ነው ፡ ፲፱ ፤ ወነለፍኩ : እንተ : ባሕረ : ኤርትራ : ወእምኔሁ : ርጉቀ : ኮንኩ ፤ ወደ : ኤርትራ : ባሕርም : ሄድሁ ፤ ከዚያም : ቦታ : የራቅሁ : ሆንኩ ፤ ፳ ፤ ወኀለፍኩ : መልዕልቶ : ለመ ልአክ : ዙጡኤል ፤ ቁጥኤልም : ይላል ፤ ዓቃቤ : ገነት ነው ፤ በሩን : ሲጠብቅ : ላዩን : አልፎት : ሄዷል ፤ ወመጻእኩ : ውስተ : ገነተ : ጽድቅ ፤ በቸርነቱም : ወደምትወረስ : ገነት : መጣሁ ፡ ፳፩ ፤ ወርኢኩ : ከሃ : ከሃቲሆሙ : ለእልኩ : ፅፅው : ዕፀወ : ብዙኃነ ፤ ከዚህ : ዕፅ : ወዲያ ፣ ወዲያ : ያለ ውን : ዕፅ : አየሁ ፤ አንድም : ከባቲሆሙ : ቢል : ከእሊህ : ዕፅ : ወዲያ ሆኜ : ብዙ : ዕፀውን : አየሁ ፣ ወዓቢያነ : ይበቍሉ : በህየ ፤ ታላላቆች : የሽቱ : እንጨቶችን በዚያ : በቅለው : አየሁ ፤ የሽቱ እንጨት : ጥቃቅን : ነው ፤ እሊህ : ግን : ታላላቆች : ናቸው ፤ ፳፪ ፤ ወእንዘ : ዔናሆሙ : ሠናይ : ዓቢያን ፤ ሽታቸውም : ያማረ : ሲሆን : ታላላቆች : ናቸው ፤ ወስናሙ : ብዙኅ ፤ ብርሃናቸውም : ብዙ : ነው ፤ ወስቡሓን ፤ ብሩሃን : ናቸው ፤ ፳፫ ፤ ወዕፀ : ጥበብ ፤ ቢበሉት : ክፉ : ጥበብ ፣ ባይበ ሉት : በጎ : ጥበብ : የሚገለጥ በት : ዕፅን : አየሁ ፤ ዘእምኔሁ : በሊያሙ : የአምርዋ : ለጥበብ : ዓባይ ፣ አዳምና : ሔዋን : ከእርሱ : በል ተው : ታላቋን : ጥበብ : የሚያወ ቁባት ፤ ወይመስል : ሐመረ : ጽራአ ፤ ተረርቃሞ : ይመስላል ፤

፰፱ ፤ ወፍሬሁኒ : ከመ : አስካለ : ወይን : ጥቀ : ሠናይ ፤
ፍሬውም : የወይን : ዘለላ : ይመስላል ፤
ወሜናሁ : ለውእቱ : ዕፅ : የሐውር : ወይበጽሕ : ነዋሀ ፤
የዚያም : እንጨት : ሽታው : ሂዶ : ከሩቅ : ይደርሳል ፤
፰፰ ፤ ወእቤ : ዝ : ዕፅ : ሠናይ : ወከመ : ሠናይ : ወፍሡሕ : ርእየቱ ፤
መልኩ : ያማረ : እንደመሆኑ ፣ ሊያውቁትም : ደስ : እንደማሰኝቱ : ይህ : እንጨት : ደስ : የሚያሰኝ : ነው : አልሁ ፤
፰፯ ፤ ወእውሥአኒ : ቅዱስ : ሩፋኤል መልአክ : ዘምስሌየ : ሀሎ ፤
ከእኔ : ጋር : ያለ : የከበረ : መልአኩ : ሩፋኤልም : መለሰልኝ ፤
፰፮ ፤ ወይቤለኒ : ዝውእቱ : ዕፀ : ጥበብ : ዘእምኔሁ : በልዑ : አቡከ : አረጋዊ ወእምከ : ዕቤራይት : እለ : ቀደሙከ ፤
ሽማግሌ : አባትህ : አዳምና : ባልቴት : እናትህ : ሔዋን : ከአንተ : አስቀድመው : የነበሩ : ከሱ : በልተው : ዓይናቸው ; የተፈታበት : ጥበብን : የሚገልፅ : ዕፀ : በለስ : ይህ : ነው ፤
የበጎ ፤ ተፈትሖ : ብሎ : ነበር : የከፉ : ሁኖባቸዋል ፤
፰፰ ፤ ወእእመርዋ : ለጥበብ : ወተፈትሐ : አዕይንቲሆሙ ፤
ከእርሱም : በልተው : ክፉ : ጥበብን : አወቁት ፣ ዓይኖቻቸውም : ተገለጡ ፤
ወአእመሩ : ከመ : ዕራቃኒሆሙ : ሀለዉ ፤
ራቁታቸውንም : እንዳሉ : ዐወቁ ፤ እንደ : ምን : መልካም ኑሮ : እንኖር : ኑሯል : ብለዋልና ፤
ወተሰዱ : እምገነት ፤
ከገነትም : ተሰደዱ : አለኝ ፤
፰፱ ፤ ወእምህየ : ሖርኩ : እስከ : አጽናፈ : ምድር ፤
ከዚያም : እስከ : ምድር : ዳርቻ : ድረስ : ሄድኩ ፤
ወርኢኩ : በህየ : አራዊተ : ዓበይተ ፤
በዚያም : ግሩማን : አራዊትን : አየሁ ፤
፱ ፤ ወይትዋለጥ : አሐዱ : እምካልኡ ፤
አንዱም : ከአንዱ : ልውጥ : ነው ፤
ወአዕዋፍኒ ፡ ይትዋለጥ : ገጸሙ : ወስኖሙ ፤
የወፎችም : ፊታቸው : ጠጉራቸውም : ይለወጣል ፤
፱፩ ፤ ወቃሉሙኒ : ይትዋለጥ : አሐዱ : እምካልኡ ፤
ቋንቋቸውም : አንዱ : ካንዱ : ይለወጣል ፤
፱፪ ፤ ወበጽባሒሆሙ : ለእሉ : አራዊት : ርኢኩ : አጽናፈ : ምድር : በጎበ : ሰማይ : የወርፍ ፤

በእኒህ : አውሬዎችም : አጠ
ገብ : በምድር : ዳርቻ : ሰማይ
በላዩ : ያረፈበት : አድማስን :
አየሁ ፤
ውኀዋኀው : ርኀዋተ፤
የተከፈቱ : ደጃፎችንም : አየሁ ፤
፱፪ ፤ ወርኢኩ : እፎ : ይወፅኡ :
ከዋክብተ : ሰማይ : ወጐሰቁ : ዘእም
ኔሁ : ይወፅኡ : ኀዋኀው ፤
ዘእምኔሁ : ይወፅኡ : ሲል : ነው ፤
ከሱ : ከዋክብት : የሚወጡበት :
ኀዋኀውን : አየሁ ፤ ከዋክብት :
የሚወጡባቸው : ደጃፎችንም :
ቆጠርሁ ፤
፱፫ ፤ ወጸሐፍኩ : ኵሎ : መዓልመ
ለለአሐዱ : አሐዱ : በበጕልቆሙ፤
የያንዳንዱን : መውጫ : ሁሉ :
በየቁጥራቸው : ጻፍሁ ፤
ወአስማቲሆሙ : በደርጎሙ ፤
ስማቸውን ፤
ወምንባሮሙ ፤
አኗኗራቸውን ፤
ወጊዜሆሙ፤
ጊዜያቸውን :
ወአውራኂሆሙ ፤
ወራታቸውን ፤
በስመ : አርአየኒ : ኡርኤል :
መልአክ : ዘምስሌየ : ሀሎ፤
ከእኔ : ጋራ : ያለ : መልአኩ :
ዑራኤል : እንዳሳየኝ : በአንድ
ነት : ጻፍሁ ፤
፱፬ ፤ ወኵሉ : አርአየኒ : ሊተ :
ወጸሐፎ፤
ሁሉንም : ለእኔ : አሳየኝ :
ጻፈው ፤
ወዓዲ፡ አስማቲሆሙ : ጸሐፈ፡ ሊተ ፤
ወጸሐፈ ፡ ሊተ : ሲል : ነው ፤
ስማቸውን : ጻፈልኝ ፤ አንድም
ወጸሐፎ : ቢል : ስማቸውን :
ጻፈው አለኝ ፤
ወትእዛዛቲሆሙ ፤
ሥርዓታቸውን ፤
ወምግባራቲሆሙ ፤
ሥራቸውን :(ምግብናቸውን) ፤
፱፭ ፤ ወእምህየ : ሖርኩ : መንገለ :
መስዕ በአጽናፈ : ምድር ፤
ከዚያም : ተነሥቼ : በምድር :
ዳር ወደ : መስዕ : ሄድኩ ፤
ወበህየ : ርኢኩ : መንክረ : ዓቢየ :
ወስዑሐ፡ በአጽናፈሃ : ለዮላ፡ ምድር፤
በዚያም : ሳለሁ : በምድር : ሁሉ :
ዳርቻ : የሚያበራ : ታላቅ : ተአ
ምራትን : አየሁ ፤
፱፮ ፤ ወበህየ : ርኢኩ : ኀዋኀው :
ሰማይ : ፍቱሐተ : በሰማይ :
ሠለስተ ፤
በመስዕ : በኩል : የተከፈቱ :
ሦስት በሮችን : አየሁ ፤
በበአሐዱ : እምኔሆሙ : ይወፅኡ :
ነፋሳት፤
ከዚያም : በየአንዳንዱ : ነፋሳት
ይወጣሉ :
፱፯ ፤ ወመንገለ : መስዕ : ሶበ :
ይነፍሕ : ቍር : ወበረድ ፤

በመስዕ : በኩል : ነፋስ : በነፈሰ
ጊዜ : ቀቅ : ክፉ : ቊር ፤
ወበረድ፤
የክፉ : በረድ ፤
ወእስሐትያ ፤
ውርጭ፤
ወሐመዳ :
ዋግ :
ወጠል ፤
ጤዛ ፤
ወዝናም ፣
የክፉ : ዝናም : ይሆናል፤
ወእምአሐቲ : ኖኅት : በሠናይ :
ይነፍሕ ፤
በአንዲቱ : መስኮት : በበጎ :
ይነፍሳል፤
፴፰ ፤ ወሶበ : በክልዔሆሙ :
ኀቍጎው ይነፍሑ : በኃይል ፤
በሁለቱ : መስኮቶች : ሁሉ :
በነፈሱ : ጊዜ : በኃይል : በር
ትተው : ይነፍሳሉ ፤
ወጸዕር : ይከውን : ዲበ : ምድር ፤
በዚህም : ዓለም : ጽኑ : መከራ
ይሆናል ፤
ወበኃይል : ይነፍሑ ፤
እነሱም : በኃይል : ይነፍሳሉ ፤
፴፱ ፤ ወእምህየ : ሖርኩ : መንገለ :
ዓረብ : በአጽናፈ : ምድር ፤
ከዚያም : ቦታ : በምድር : ዳርቻ :
ወደ : ፀሐይ : መግቢያ : ሄድኩ :
ወርኢኩ : በህየ : ሠለስተ : ኀዋኀወ :
ርኅዋተ : በከመ : ርኢኩ : በምሥ
ራቅ : በአምጣነ : ኀዋኀው : ወበአምጣነ :
መፃኡ ፤
በምሥራቅ : በኩል : ባሉት :
ኀዋኀው : መጠን : በመውጫው :
ልክ : የተከፈቱ : ሦስት : መስኮ
ቶችን : አየሁ :
፵ ፤ ወእምህየ : ሖርኩ : መንገለ :
ዓዜብ : በአጽናፈ : ምድር ፤
ከዚያም : ቦታ : በምድር : ዳርቻ :
ወደ : አዜብ : ሄድኩ ፣
፵፩ ፤ ወበህየ : ርኢኩ : ፫ተ : ኀዋ
ኀወ : ሰማይ : ርኅዋተ ፤
በዚያም : ቦታ : የተከፈቱ :
ሦስት : የሰማይ : መስኮቶችን :
አየሁ ፤
ወይወፅእ : እምህየ : አዜብ ፤
በዚያም : ቦታ : ውዑይ : ነፋስ :
ይነፍሳል፤
ወጠል : ወዝናም : ወነፋስ ፤
ጤዛ ፣ ዝናም ፣ ነፋስ : ይነፍሳል፤
፵፪ ፤ ወእምህየ : ሖርኩ : መንገለ :
ጽባሕ በአጽናፈ : ሰማይ ፤
ከዚያም : ቦታ : ተነሥቼ : በሰማይ
ዳርቻ : ወደ : ፀሐይ : መውጫ :
ሄድኩ : ከዚህ : እንደ : አርእስት :
ተናግሮታል : ኋላ : በደግ : ያመ
ጣዋል ፤
ወበህየ : ርኢኩ : ሠለስተ : ኀዋኀወ :
ሰማይ : ርኅዋተ : መንገለ : ጽባሕ ፤
በዚያም : ቦታ : ሳለሁ : በፀሐይ :
መውጫ : በኩል : የተከፈቱ :
ሦስት የሰማይ : ደጃፎችን :
አየሁ ፤

፰ ፤ ወበላዕሌሆሙ : ጎዋጎው : ንኡሳን : በበአሐዱ : እምእልኩ : ጎዋጎው : የኃልቆ : ንኡሳን : ከዋክብተ : ሰማይ ፤
በታናናሾቹ : ደጃፎችም : ላይ : ከእነዚህ : ደጃፎች : በያንዳንዱ ታናናሾች : የሰማይ : ኮከቦች : ይገቡበታል ፤ መስኩቶችስ : ዓቢያን : ናቸው ፤ ንኡሳን : ከዋክብት : ስለወጡባቸው : ስለገቡባቸው : ንኡሳን : አሳቻው ፤
፱ ፤ ወየሐውሩ : ምዕራብ : በፍኖት : እንተ : ተርእየት : ሎሙ ፣ ተሠርዐት : ሎሙ : ሲል : ነው ፤ በተሠራችላቸው ፤ አንድም : እንደ : ንባቡ : ተርጉም ፣ እኔ : ባየሁላቸው : ጕዳና : ወደፀሐይ : መግቢያ : ይሔዳሉ ፤
፲ ፤ ወሶበ : ርኢኩ : ባረኩ ፤ ይህንም : በአየሁ : ጊዜ : አመሰገንሁ ፤
ወበእሉ : ጊዜ : እባርክ : ለእግዚአ : ስብሐት ፤
በየጊዜውም : የክብር : ባለቤት : ጌታን : አመሰግነዋለሁ ፤
ዘንብረ : ተአምራተ : ዓቢያነ : ወስኩሓነ : ከመ : ያርኢ : ዕበየ : ግብሩ : ለመላእክቲሁ : ወለነፍሳተ : ሰብእ ፤
የፍጥረቱን : ገናንነት : ለሰው ችና : ለመላእክት : ሲገልጥ ፤ የክብር : ባለቤት : ጌታንም : በየጊዜው : አመሰግነዋለሁ :
፲፩ ፤ ከመ : ይሰብሑ : ግብሮ ፤ ሥራውን : ያመሰግኑ : ዘንድ ፤ ወኮሉ : ተግባሩ : ከመ : ይርአዩ : ግብረ : ኃይሉ ፤
ፍጥረቱም : ሁሉ : የኃይሉን : ሥራ : ያዩ ዘንድ ፤
ወይሰብሕም : ለግብረ : እደዊሁ : ዓቢይ ፤
ታላቅ : የሆነ : የከሃሊነቱንም : ሥራ : ያመሰግኑ : ዘንድ ፤
ወይባርክም : እስከ : ለዓለም ፤
ስነ : ፍጥረቱም : እሱን : ለዘለዓለሙ : ያመሰግኑት : ዘንድ : ይህንን : አደረገ ::

ምዕራፍ ፱
ጉባኤ

፩ ፤ ራእይ : ዘርእየ : ካልአ : ራእየ : ጥበብ : ዘርእየ : ሄኖክ : ወልደ : ያሬድ ፤
ራእይና : ራእይ ፣ ዘርእየና : ዘርእየ : ሄኖክ : አንድ : ወገን ፤ ሄኖክ : ያየው ራእይ : ይህ : ነው ፤ አንድም : ካልአ : ራእየ : የያሬድ : ልጅ : ሄኖክ : በሌላ : ጊዜ : ያየው : ራዕይ : ይህ : ነው ፤
ወልደ : መላልኤል ፤
ያሬድን : የመላልኤል : ልጅ : አለው ፤
ወልደ : ቃይናን ፤
መላልኤልን : የቃይናን : ልጅ : አለው ፤
ወልደ : ሄኖስ ፣

ቃይናንን : የሄኖስ : ልጅ : አለው ፤
ወልደ፡ ሴት ፣
ሄኖስን ፡የሴት : ልጅ : አለው : ወልደ : አዳም ፤
ሴትን : የአዳም : ልጅ : አለው ሽቅብ : ይቆጥራል ፤
፱ ፤ ወዝ ፡ ርእሱ ፡ ለነገረ ፡ ጥበብ ፤ ግብረ : ጥበብ : ሲል ፡ነው ፤ ዘአንሣእኩ ፡ እትናገር ፤
በዚህም : ዓለም : ላሉ : ሰዎች እናገር : ዘንድ : የጀመርኹት : የዘጠኙ : ሕገጋት : አበጋዝ : ኢታምልክ : ይህ : የጥበብ : ነገር : መጀመሪያና መጨረሻ : ነው ፤
ወእብል : ለእሰ : የኀድሩ : ዲበ : የብስ ፤
በዚህ : ዓለም : ላሉ፡ ለምች ፡እና ገር : ዘንድ : አበው : ስሙ ፤
፲ ፤ ስምዑ ፡ ቀደምት፤ ወርእዩ ፡ ደኃርያን ፡ ነገረ ፡ ቅዱሰ፤
በኋላም : የተነሣችሁ : ውሉድ የምናገረውን : ስሙ ፤ ይህን : ልዩ : ነገር : ስሙ ፤
እለ ፡ እነግር ፤ ቅድመ : እግዚአ : መናፍስት ፤
እግዚአ : መላእክት ፣ እግዚአ ሀብታት ፣ እግዚአ : ነፋሳት ፣ እግዚአ፡ ነፍሳት፡ ሲል : ነው ፤
መላእክት : ከጌታ : ፊት : የም ናገረውን ፣ የከበረ : የኢታም ልክን : ነገር : አስተውሉ ፤
፲፩ ፤ እሱ ፡ ቀዳሚ ፡ ይኄይስ ፡ ብሂል ፤ ነገሮሙ፡ ለእሱ : ሲል : ነው ፤ የአበው : ነገራቸው : ከዘጠኙ : ሕገጋት : ኢታምልክ : ይበል ጣል : ማለት : ነው ፤
ወደኃርያንሂ : ኢንክልእ : ርእሳ : ለጥበብ ፤
ደኃርያን : ውሉድም ፡ ከዘጠኙ ፡ ሕገጋት : ኢታምልክ : ትበልጣ ለች : ማለትን : አንከለክልም ፤
አንድም : እሱ : ቀደምት : ይኄ ይሱ : ብሂል : ነገርየ ፡ ይላል ፤ የእኔ : ነገሬ ፡ አበው : ኢታምል ክን ፡ በመጠበቅ : ይበልጡናል : ማለት : ነው ፤
ወደኃርያንሰ ፡ ኢንክል ፤
ደኃርያን : ውሉድ : እኛ : ግን የዘጠኙ : አበጋዝ : ኢታምልክን መጠበቅ : አንችልም ፤
፲፪ ፤ ወእስከ ፡ ይእዙ ፡ ኢተውህበኒ ፡ እምቅድመ : እግዚአ : መናፍስት : ዘነሣእኩ ፡ ፍበበ ፡ ዘከመ : ሐለይኩ : በከመ : ፈቀደ : እግዚአ : መናፍስት ዘተውህበኒ ፡ እምኔሁ ፤
ጥበብን : የተቀበልሁት : መቀ በል ፤ አንድም : በጥበብ : የተቀ በልሁት ፤ አንድም ፡: ጥበብ ፡ ቢል ፡ የተቀበልሁት ፡ ጥበብ ፣ እኔ ፡ እንደ ወደድሁ ፡ እንደ : አሰብሁ : እስከ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ በእግዚአ ፡ መናፍስት፡ ፊት : አልተሰጠኝም ፤
ክፍለ : ሕይወት : ዘለዓለም ፤
የዘለዓለም : ዕድል : የሚሆን :

ከእግዚአ : መናፍስት : የተሰ
ጠኝ : ጥበብ : እስከ : ዛሬ :
ድረስ : አልተሰጠኝም ፤
፯ ፤ ወኮነ : ብየ : ፫ቱ : ምሳሌያት፤
ሦስቱ : ነገራት : ተገለጹልኝ ፤
ሁለቱ : ነገራት : ናቸው ፤ አንዱ :
ምሳሌ : ነው ፤ ከዚያም : ነገር :
አለበት ፤ አጸምዕ : ምሳሌ :
በእዘንየ፞ : እንዲል ፤
፯ ፤ ወአንለ : እብሎሙ : ለእለ :
የኀድሩ : ዲበ : የብስ ፤
እኔም : በዚህ : ዓለም ፡ ላሉ :
ሰዎች : እነግራቸው : ጀመር ፤
፰ ፤ ምሳሌ : ቀዳሚ : ሶበ : ያስተ
ርኢ : ማኅበረ : ጻድቃን ፤
መጀመሪያው : ነገር : ይህ :
ነው ፤ የደጋጎች : ማደሪያ :
በተገለጠ : ጊዜ ፤
ወይትኬነኑ : ኃጥአን : በኃጢአቶሙ፡
ኃጥአንም : በኃጢአታቸው :
በተፈረደባቸው : ጊዜ ፤
ወእምገጸ : የብስ : ይትሐወኩ ፤
ከዚህ : ዓለም : ይጠፋሉ ፤
፱ ፤ ወሶበ : ያስተርኢ : ጻድቅ :
በገጸሙ : ለጻድቃን : እለ : ኀሩያን :
ተግባሮሙ : ስቁል : በእግዚአ : መና
ፍስት ፤
ጻድቀ : ባሕርይ : ክርስቶስ :
ጌታ : ለእነርሱ : ያደረገው : ነገር :
በጸናላቸው : ጊዜ ፤ አንድም :
እነርሱ : ለእርሱ : ብለው :
ያደረጉት : በጸናላቸው : ጊዜ ፤

፩ ፤ ወያስተርኢ : ብርሃን : ለጻድቃን፡
ወለኀሩያን : እለ : የኀድሩ : ዲበ :
የብስ ፤
በዚህ : ዓለም : ለሚኖሩ : ለደ
ናግልና : ለሕጋውያን : ብርሃነ :
መለኮቱ : በተገለጠ : ጊዜ ፤
፲፩ ፤ አይቱ : ማኅደረ : ኃጥአን :
ወአይቱ : ምዕራፎሙ : ለእለ :
ከሀድም : ለእግዚአ : መናፍስት ፤
የነፍሳት : ጌታን : የካዱት : ሰዎች :
ቦታቸው : ወዴት : ነው ? የኃጥአን፡
ማደሪያቸውስ : ወዴት : ነው ?
፲፪ ፤ እምኀየሶሙ : ሶበ : ኢተወ
ልዱ ፤
ጥንቱን : ባይፈጠሩ : በተሻላ
ቸው : ነበር ፤
ወሶበ : ይትከሠታ : ኅቡዓቲሆሙ :
ለጻድቃን : ይትኬነኑ : ኃጥአን ፤
ሰውረው : ያደረጉት ፤ አንድም
ሰውሮ : ያደረገላቸው : የጻድ
ቃን : ክብራቸው : በተገለጠ :
ጊዜ ፤ በኀጢአተኞች : ይፈረ
ድባቸዋል ፤
ወይትህወኩ : ረሲዓን : እምገጸ :
ጻድቃን : ወኀሩያን ፤
ደናግልንና : ሕጋውያንን : ከመ
በደላቸው የተነሣ : ሕግን :
የዘነጉ : ሰዎች : ይታወካሉ ፤
፲፫ ፤ ወእምይእዜ : ኢይክውኑ : እዘ
ዛን : ወኢልዑላን : እለ : ይእኀዝዋ :
ለምድር ፤
እንግዲህ : ወዲህ : ይህችን :
ዓለም : የሚገዙ : ሰዎች :

፩ መዝ. ፸፰ ፥ ፬

ከዛሬ : ጀምሮ : ጽኑዓን : ክቡራን : አይሆኑም ፤

፲፩ ፤ ወኢይክሉ : ርእየ : ገጸ : ቅዱሳን ፤

የቅዱሳንን : ፊት : ሊያዩ : አይችሉም :

እስመ : ለእግዚአ : መናፍስት : ተርእየ : ብርሃኑ : ለገጸ : ቅዱሳን : ጻድቃን : ወጎሩያን ፤

ለደናግልና : ለከበሩት : ሕጋውያን: የመላእክት :ጌታ : ብርሃኑ: መለኮቱ ፤ አንድም : የባሕርይ : ክብሩ : ተገልጿልና : የቅዱሳንን: ፊት : ማየት : አይችሉም ፤

፲፪ ፤ ወነገሥት : አዚዛን : በውእቱ : ጊዜ : ይትነጉሉ : ወይትወሀቡ : ውስተ : እደ : ጻድቃን : ወቅዱሳን ፤

በጻድቃን : እጅ : የሚፈረድባቸው : ሆኖ : አይደለም ፤ ጻድቃንን : በበደሉበት : በደል : የሚፈርድባቸው : ስለሆነ ፤

፲፫ ፤ ወእምህየ : አልቦ : ዘያስተምህር : ሎሙ : ኀበ : እግዚአ : ስብሐት : እስመ : ተወድአ : እንቲአሆሙ : ሕይወት ፤

የእነርሱ : የሚሆን : ደኅንነታቸው : ጨርሶ : ጠፍቷልና : ከዚያ : ከመከራው : በመላእክት ጌታ : ዘንድ : ለእነርሱ : የሚያማልድ : የለም ፤

፲፬ ፤ ወይከውን : በዝንቱ : መዋዕል : ይወርዱ : ደቂቀ : ጎሩያን: ወቅዱሳን : እምልዑላን : ሰማያት ፤

በዚያ : ወራት : እንዲህ : ይሆናል ፤ ከልዑል : መዓርግ ፣ ከደብር : ቅዱስ ፣ ከሰማያዊ : ግብር : የወረዱ : ደቂቀ : ሴት ገሃነም : ይወርዳሉ ፤

ወአሐደ : ይከውን : ዘርዖሙ : ምስለ ውሉደ : ሰብእ ፤

ልጆቻቸው : ከቃየል : ልጆች : ጋር : አንድ : ይሆናሉ ፤

፲፭ ፤ ወበውእቱ : መዋዕል : ነሥአ : ሄኖክ : መጻሕፍተ : ቅንአት ፤ ወመዓት ፤ ባልንጀራ : ለባልንጀራው : ቀንቶ : የሚሠራው : ኃጢአት : የተጻፈበት ፤ አንድም : ለአምላክነቱ : ቀንቶ : የሚያመጣው : መቅሠፍት : የተጻፈበት :

ወመጻሕፍተ : ጕጕዓ : ወሀውክ ፤

ለሞት : ለመከራ : የሚያስቸኩል : መከራ : የተጻፈበትን : መጽሐፍ : ሄኖክ : አነሣ ፤

፲፮ ፤ ወምሕረት : ኢይከውን : ላዕሌሆሙ : ይቤ : እግዚአ : መናፍስት ፤ የመላእክት : ጌታ : ይቅርታ : አያደርግላቸውም : አለ ፤

፳ ፤ ወበውእቱ : ጊዜ : መሠጠኒ : ደመና : ወአውሶ : ነፋስ : እምገጸ : ሰምድር ፤

በዚያም : ጊዜ : ጥቅል : ነፋስና : ደመና : ከዚህ :ዓለም : ወሰዶ ፤

ወእንበረኒ: ውስተ : ጽንፈ: ሰማያት ፤

በሰማይ : ዳርቻ : በአድማስ : አኖረኝ :

፰፩ ፤ ወበህየ : ርኢኩ : ካልአ : ራእየ፣

በዚያም : ቦታ : ሴላ : ራእይ : አየሁ ፤

ማኅደሪሆሙ : ለጻድቃን : ወምስካባቲሆሙ : ለቅዱሳን ፤

የጻድቃንን : ማደሪያቸውን : የቅዱሳንን : ቦታቸውን : አየሁ ፤

፰፪ ፤ ወበህየ : ርእያ : አዕይንትየ : ማኅደሪያሆሙ : ምስለ : መላእክት ፤

ከዚያም : ቦታ : ዓይናቼ : ከመላእክት : ጋራ : የሚኖሩበት ማደሪያቸውን ፣ ወምስካባቲሆሙ፡ ምስለ : ቅዱሳን ፤ ከቅዱሳንም : ጋራ : የሚኖሩበትን : ቦታቸውን : አዩ ፤

፰፫ ፤ ወይስእሉ : ወያስተብቍዑ : ወይጸልዩ፡ በእንተ : ውሉደ : ሰብእ ፣

ስለ : ሰውም : ልጆች : ፈጽመው፡ ይለምናሉ : ይማልዳሉ ፣ ይጸልያሉ ፤

፰፬ ፤ ወጽድቅ : ከመ : ማይ : ይውኅዝ : በቅድሜሆሙ ፤

ቸርነት : በፊታቸው : እንደ : ውሀ : ይፈስሳል ፡ (በዝቶ : ይሰጣል) : ሲል : ነው ፤

ወምሕረት ከመ : ጠል : ውስተ : ምድር ፤

ይቅርታም : በዚህ : ዓለም : እንደ : ጠል : ይሆናል ፣ በዝቶ ይሰጣል ፤

ከመዝ : ውእቱ : ማዕከሌሙ : ለዓለመ : ዓለም ፤

ጻድቃን ፣ መላእክት ፣ በሚያማልዱት : ምልጃ : ራሳቸውንም፣ ሰውንም : ጠቅመው : ለዘላለሙ : ይኖራሉና ፤

፰፭ ፤ ወበውእቱ : መዋዕል : ርእያ፡ አዕይንትየ : መካነ : ኀሩያን : ዘጽድቅ ወዘሃይማኖት ፤

በምግባር : በሃይማኖት : ጸንተው : የሞቱ : የጻድቃንን : ቦታ : አየሁ ፤

፰፮ ፤ ወጽድቅ : ይከውን : በመዋዕሊሆሙ : ለጻድቃን : ወለኀሩያን : አልዖሙ : ጕልቍ : ቅድሜሁ : ለዓለመ : ዓለም ፤

በዘመናቸው : ቸርነቱ : ይደረግላቸዋል ፤ ለተመረጡ : ጻድቃን : ለሚኖሩት : ዘመን : ፍጻሜ : የለውም ፤ አንድም : ለጻድቃን: ቍጥር : የላቸውም :

፰፯ ፤ ወርኢኩ : ማኅደሮሙ : መትሕተ : አክናፈ : እግዚአ : መናፍስት፤

በእግዚአ : መናፍስት : አጠገብ የተያዘ፡ ማደሪያቸውን : አየሁ ፤

፰፰ ፤ ወሰኰሙ : ጻድቃን : ወኀሩያን : በቅድሜሁ : ይትለሐዩ : ከመ : ብርሃነ : እሳት ፤

ያበርሁ : ሲል : ነው፤ ደናግልና ሕጋውያንም : ሁሉ : በፊቱ : እንደ : መንፈስ : ቅዱስ : ብርሃን : ያበራሉ ፤

፰፱ ፤ ወአፋሆሙ : ይመልዕ : በረ
ከተ : ወከናፍሪሆሙ : ይሴብሕ :
ስሞ : ለእግዚአ : መናፍስት : ወጽ
ድቅ ፤
አፋቸው : በረከትን : (ምስጋናን)፡
ይመላል ፣ ከንፈሮቻቸውም :
የመላእክት : ጌታን : ስም :
ያመሰግናሉ ፤ አንድም : ስሙን፡
ያመሰግኑት ፤ ዘንድ ፣ አንድም :
በስሙ : አምነው : ያመሰግኑት፡
ዘንድ ፤
፱ ፤ ወጽድቅ : ቅድሜሁ : ኢየሐ
ልቅ ፣
በፊቱ : የሚሰጥ : ቸርነት : እያ
ልቀም :
ወርትዕ : ቅድሜሁ : ኢየሐልቅ ፤
በርትዓተ : ሕሊና : የሚገኘው :
ክብርም : በፊቱ : ፍጻሜ : የለ
ውም ፤
፲፩ ፤ ወበህየ : ፈቀድኩ : እኅድር :
ወፈተወቶ : ነፍስየ : ለውእቱ :
ማኅደር፤
በዚያም : ቦታ : እኖር : ዘንድ
ወደድሁ ፣ ያንንም : ቦታ :
ልቡናዬ : ወደደችው ፤
፲፪ ፤ በህየ : ኮነ : ክፍልየ : ቅድመ፤
እኔ : በከንቱ : እንዲህ : አልሁ፡
እንጂ : ጥንቱም : ዕድል : ፈን
ታዬ : በዚህ : ሆነ ፤
እስመ : ከመዝ : ጸንዐ : በእንቲአየ :
በቅድመ : እግዚአ : መናፍስት ፤
በመላእክት : ጌታ ፈቃድ :
ስለእኔ : መንግሥተ : ሰማይ :
ጸንቷልና ፤ እስመ : በእንቲአክሙ :
ፈጠርክም : ለዓለም : እንዲል :
፲፫ ፤ ወበውእቶን : መዋዕል : ሰባ
ሕኩ : ወአልዐልኩ : ስሞ : ለእግዚአ፡
መናፍስት ፤
በዚያም : ወራት : የመላእክት
ጌታን : ስም : አከብሬ : አመ
ሰገንኩ ፤
በረከተ : ወስብሐተ : ወሀብኩ ፤
እስመ : ውእቱ : አጽንአኒ : በበረከት
ወስብሐት : በክመ : ፈቃዱ :
ለእግዚአ : መናፍስት ፤
የመላእክት : ጌታ : እንደ :
ወደደ ፤ በፍጹም : ምስጋና :
እርሱ : አጽንቶኛልና : ፍጹም :
ምስጋናን : አቀረብሁ ፤
፲፬ ፤ ወኮንዱየ : ርእያ : አዕይንትየ፡
በውእቱ : መካን ፤
ዓይኖቼ : ቅዝ : ብለው : ያያሉ
እንደ : ገጠር : ሰው ፣ ከተማ :
ሚዶ : ቅዝ : ብሎ : እንዲያይ ፤
፲፭ ፤ ወባረክም : ወሰባሕክም :
እንዘ : እብል : ቡሩክ : ውእቱ :
ወይትባረክ : እምቅድመ : ዓለም :
ወእስከ፡ ለዓለም ፤
የተመሰገነ : ነው ፤ ከጥንት :
ጀምሮ : እስከ : ዘለዓለሙ :
ይከበር : ይመሰገን : እያልኩ :
ፈጽሜ : አመሰገንሁት፤
፲፮ ፤ ወበቅድሜሁ : አልቦ : ማኅለ
ቅት ፤
በፊቱም : ለሚደረገው : ቸርነት
ፍጻሜ : የለውም ፤

፱፤ ፤ ውእቱ : የአምር : ዘእንበለ : ይትፈጠር : ዓለም : ምንት፡ ውእቱ፡ ዓለም ፤
ዓለም : ሳይፈጠር : ይህ : ዓለም : ምን : እንደሆነ : እርሱ : ያውቃል ፤ ወለትውልደ : ትውልድ : ዘይከውን : ለልጅ : ልጅ : ዘመን : የሚሆ ነውን : ነገር : ያውቃል ፤
፲፤ ፤ ይባርኩከ : እለ : ኢይነውሙ : ወይቀውሙ : በቅድመ፡ ስብሐቲከ ፤ የማያርፉ ፤ በጌትነትህም : ፊት፡ የሚቆሙ : መላእክት : ያመሰ ግኑሃል፤
፲፩ ፤ ወይባርኩ : ወይሴብሑ : ወያሴዕሉ : እንዘ : ይብሉ : ቅዱስ : ቅዱስ፡ ቅዱስ፡ እግዚአ : መናፍስት፤ የመላእክት : ጌታ : ንጹሕ ፣ ክቡር : ልዩ : አንተ : ነህ : እያሉ : ፈጽመው : ያመሰግናሉ፡ ከፍ : ከፍም : ያደርጋሉ ::
ቅዱስ ፣ ቅዱስ ፣ ቅዱስ : ብሎ ሦስትነቱን ፣ እግዚአ : መናፍ ስት : ብሎ : አንድነቱን : ተናገረ ፤ አንድም : ቅዱስ : ብሎ : ፮ነቱን : ተናገረ ፤ ለፎቱ : ሁሉ : ልብ : ቃል : እስትንፋስ : ቢኖራቸው : ቅዱሳን : ቅዱሳን : ባለ : ነበርና : ቅዱስ : ቅዱስ : ቅዱስ : ብሎ : ፫ት : ጊዜ : መናገሩ : የ፫ነቱ : ነው ፤
ወይመልእ : ምድረ : መናፍስት ፤ ፍጥረታት : ያሉባትን : ምድር በምልዓት : ይመላል ፤ አንድም፡ ምድረ : መናፍስተ : ቢል : ፍጥረታትን : በምድር : ይመ ላል፤ አንድም : ምስጋናን : በምድር : ይመላል ፤
፶፤ ወበህየ : ርእያ : አዕይንትየ : ኵሉ : እለ : ኢይነውሙ : ይቀውሙ : ቅድሜሁ : ወይባርኩ ፤
በዚያም : ቦታ : የማያርፉ : መላእክትን : ሁሉ : በፊቱ : ቁመው : ሲያመሰግኑ : ዓይኖቼ : አዩ ፤
፶፩ ፤ ወይብሉ : ቡሩክ : አንተ : ወቡሩክ : ስመ : ለአግዚአ : መናፍስት : ለዓለመ : ዓለም ፤ አንተ : የከበርክ : ነህ ፤ የመላ እክት : ጌታ : ስሙም : ለዘለ ዓለም : የከበረ : ነው : ይላሉ ፤
፶፪ ፤ ወተወለጠ : ገጽየ : እስከ : ስእንኩ : ነጽሮ ፤
ቀና : ብሎ : ማየት : እስኪሳ ነኝ : ድረስ : ዓይን : ልቡናዬ : ተሰወጠ ::

ምዕራፍ ፲

፩ ፤ ወርኢኩ : እምድኅረዝ : አእ ላፈ አእላፋት : ወትእልፊተ : አእላ ፋት፤
ከዚህም : በኋላ : ፈጽመው : የበዙ : የብዙ : ብዙ : የሚሆኑ መላእክትን : አየሁ ፤
ወአልቦሙ : ጕልቍ : ወሐሳብ : ለአለ : ይቀውሙ : ቅድመ : እግዚአ መናፍስት፤